IslamHouse.com

Osoul Center

# فصول في العقيدة

## (الرسالة الشامية)

# በዐቂዳ ዙሪያ የተጻፉ ክፍሎች

ዝግጅት፡

ዐብዱል ዐዚዝ ቢን መርዙቅ አጥ-ጠሪፊ

ትርጉም፡

ዑስታዝ ጋሊ. አባቦር አባጉማ

ዑስታዝ ሐቢብ አሕመድ

አርማች_

ሼኽ ጀማል ሼኽ ሙሐመድ አህመድ

Amharic
አማርኛ
أمهرية

Amharic
አማርኛ
أمهري

# فصول في العقيدة

## (الرسالة الشامية)


المؤلف

**عبدالعزيز بن مرزوق الطريفي**

ترجمة

الداعية  غالي أبابورأباغوما

والداعية حبيب أحمد

المراجعة

الداعية جمال محمد أحمد

Osoul Center

أُعد هذا الكتاب وصمِّم من قبل مركز أصول، وجميع الصور المستخدمة في التصميم يملك المركز حقوقها، وإن مركز أصول يتيح لكل مسلم طباعة الكتاب ونشره بأي وسيلة، بشرط الالتزام بالإشارة إلى المصدر، وعدم التغيير في النص، وفي حالة الطباعة يوصي المركز بالالتزام بمعاييره في جودة الطباعة.

+٩٦٦ ٥٠ ٤٤٤ ٢٥٣٢
+٩٦٦ ١١ ٤٤٥ ٤٩٠٠

+٩٦٦ ١١ ٤٩٧ ٠١٢٦

ص. ب. ٢٩٤٦٥ - الرياض ١١٤٥٧

osoul@rabwah.com

www.osoulcenter.com




በአሏህ ስም እጅግ በጣም
ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ
በሆነው

| | | |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 9 |
| 2 | ክፍል አንድ | 13 |
| 3 | ክፍል ሁለት | 17 |
| 4 | ክፍል ሦስት | 19 |
| 5 | ክፍል አራት | 23 |
| 6 | ክፍል ስድስት | 27 |
| 7 | ክፍል ሰባት | 31 |
| 8 | ክፍል ስምንት | 35 |
| 9 | ክፍል ዘጠኝ | 39 |
| 10 | ክፍል አስር | 43 |
| 11 | ክፍል አስራ አንድ | 47 |
| 12 | ክፍል አስራ ሁለት | 49 |
| 13 | ክፍል አስራ ሦስት | 51 |
| 14 | ክፍል አስራ አራት | 53 |
| 15 | ክፍል አስራ አምስት | 57 |
| 16 | ክፍል አስራ ስድስት | 59 |

# መግቢያ

إن الحمد لله نحمده، ونستعينه، ونعوذ بالله من شرور أنفسنا وسيئات أعمالنا، من يهده الله فلا مضل له، ومن يضلل فلا هادي له

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይገባው፡፡ እናመሰግነዋለን፤ እርዳታም ከሱ እንጠይቃለን፡፡ ከነፍሳችን ክፋትና ከስራዎቻችን ጥፋት በአላህ እንጠበቃለን፡፡ አላህ የመራውን ሰው የሚያጠመው ነገር የለም፤ አላህ ያጠመመውን ደግሞ የሚመራው የለም፡፡ ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ እንደ ሌለ፤ እሱ ብቸኛ ነው አምሳያ የለውም፡፡ ሙሐመድም (ሰዐወ) የአላህ ባርያና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡

ውዳሰው ተቆጥሮ ለማይዘለቀው አላህ ምስጋና ይገባው፡፡ ቱሩፋት ሁሉ መጀመርያውም መጨረሻውም የሱ ነው፡፡ ከአላህ ውጪ በሐቅ የምመለክ አምላክ እንደለሌ እመሰክራለው፡፡ አቻ እና አምሳያ የለውም፡፡ ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) የአላህ ባሪያ እና መልክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለው፡፡

በመቀጠል ይህቺ አጠር ያለች የዐቂዳ ማብራሪያ መጽሐፍ ስትሆን በተናጠል ለሻም ሰዎች ያዘጋጀዋት ነች፡፡ እነርሱም ክርስትያኖች እና የተለያዩ የውስጥ ድርጅቶች ለአንድ ክፍለ ዘመን ያህል ከተቆጣጠሩዋት ቡኃላ ሀገራቸውን እና ምድራቸውን ዳግም ይወርሳሉ፡፡ ይህንንም ተከትሎ በእስላም መሠረታዊ ነገሮችና ቅርንጫፎች ላይ በርካታ ተጽእኖዎች ደርሰዋል፡፡

ይህንንም ተከትሎ በርካታ የሀገሪቷ ነዋሪዎች እና የውጭ ሀገር ዜጎች አንድ ባሪያ ነገ የአላህን ሐቅ አስመልክቶ የምጠየቅበትን መልስ እንድያዘጋጅላቸው ጠይቀውኝ ነበር፡፡ የአላህ ሐቅ ያልነውም ያ አላህ ለኑሕ እና ከእርሱ ቡኃላ ላሉ ነቢያት (ሰ.ዐ.ወ) እንድተገብሩት ያዘዘው እና የእስላም መልዕክት መደምደሚያ ሆኖ በማይጽፉት እና በማያነቡት ነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የመጣው ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿شَرَعَ لَكُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِۦ نُوحًا وَٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ وَمَا وَصَّيۡنَا بِهِۦٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓۖ أَنۡ أَقِيمُواْ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُواْ فِيهِ﴾ [الشورى: ١٣]

ለናንተ ከሃይማኖት ያንን በርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፤ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን. ያንንም በርሱ ኢብራሂምን ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን. ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ. በርሱም አትለያዩ. ማለትን (ደነገግን)፡፡ *(አል-ሹራ፡ 13)*

ነፍስ ደስ የሚያሰኛትን ነገር መከተል በበዛ ቁጥር ስሜቶችንም መከተል እየበዛ መጣ፡፡ ስሜቶችን መከተል ስበዛም የአመለካከት ልዩነቶችም እየበዙ መጡ፡፡ የአመለካከት ልዩነቶችም ስበዙ የተለያዩ ቡድኖች እየተፈጠሩ መጡ፡፡ ዐረቢኛ ቋንቋ በዐረቦች እና ከዐረብ ውጪ ያሉ ሰዎች ዘንድ እየተዳከመ ስመጣ የአላህን ስሞች እና ባህሪያቶችን አስመልክቶ አጣሞ መተርጎም እና ሌሎች በሰው ላይ በምመሳሰሉ አሻሚ በሆኑ ነገሮች መብቃቃት ቀላል እየሆነ መጣ፡፡ ከቁርኣን አንቀጽና ከሐዲስም መረጃ የመሳሰሉ ነገሮችን ማቅረብ ቀላል ሆነ፡፡

የመጀመሪያዎቹ ቡድኖች በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የተገኙ ስለሆነ ከእነርሱ ቡኃላ ለመጡት ደግሞ ጉዳዩ ቀላል ሆነላቸው፡፡ ምክንያቱም አሻሚ የሆኑ ነገሮችን እና ስሜቶችን መከተል እስካለ ድረስ ጉዳዩ ከእነርሱ ቡኃላ ለምመጡ ሰዎች ይበልጥ ቀላል እና ገር ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ሹብሃ በራሱ መጀመርያ ስሜት ነው፡፡ ከዚያም አሻሚ ነገር (ሹብሃ) ትሆናለች፡፡ ከዚያም ሰዎች የሚከተሏት መንገድ ትሆናለች፡፡ ከዚያም ሰዎች መጀመሪያ ምን እንደሆነች ሳያውቁ መጨረሻ ላይ ባገኟት ሁኔታ ላይ ይከተሏታል፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿أَفَكُلَّمَا جَآءَكُمْ رَسُولٌۢ بِمَا لَا تَهْوَىٰٓ أَنفُسُكُمُ ٱسْتَكْبَرْتُمْ فَفَرِيقًا كَذَّبْتُمْ وَفَرِيقًا تَقْتُلُونَ﴾ [البقرة: ٨٧]

ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር **(**ከመከተል**)** ትኮራላችሁን ከፊሉን አስተባበላችሁ፤ ከፊሉንም ትገድላላችሁ፡፡ *(አል-በቀራ፡ 87)*

መጀመርያ ስሜትን ነገረን፡፡ ከዚያም ወደ ኩራት ከዚያም ወደ ማስተባበል በመጨረሻም ወደ ጠላትነት ይለወጣል፡፡ የተለያዩ ሀይማኖቶችና የተሳሳቱ ሃሳቦች በሁሉም ህዝብ ውስጥ በዚህ ሁኔታ ይከሰታል፡፡

አላህ ሐቅ እና መመርያን በመልዕክተኛው (ሰዐወ) ላይ አወርዷል፤እንግዲያውስ ንፁውን የፈለገ ሰው የሰዎች አዕምሮ ሳያደፈርሰው ከመጀመሪያው ምንጩ ይውሰድ፡፡ መለኮታዊ ራእይ እንደ ውሃ ሲሆን አዕምሮ ደግሞ እንደ ዕቃ ነው፡፡ አላህ ራእይን አውርዶ በመልክተኛው ልብ ላይ አስቀመጠ፤ከዚያም ነቢዩ ደግሞ በሰሓቦች ልብ ውስጥ አስቀመጡ፤ሰሐቦች ደግሞ በታቢዒዮች ልብ ውስጥ አስቀመጡ፡፡ ከአንድ እቃ ወደ ሌላ እየተገለበጠ ሲሄድ መደፍረስም እየጨመረ ይመጣል፡፡ ስለዚህ ይበልጥ ትክክል እና ንጹህ የሆነው ዕቃ የመጀመሪያው ሲሆን እርሱም የነቢዩ (ሰዐወ) ቀልብ ነው፤ ቀጥሎም የሰሓቦች ነው፡፡

ሙስሊም ሰሒሕ በሆነ ኪታባቸው ከአቡ ሙሳ (ረ.ዐ) በዘገቡት እንዲህ ይላል፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ አሉ፡

‹‹እኔ ለሠሓቦቼ ደህንነት ነኝ፤ በሄድኩ ጊዜ ሰሓቦቼ ላይ (ከፈተና) የተቀጠሩት ነገር ይመጣባቸዋል፤ ሰሓቦቼ ለህዝቦቼ ደህንነት ናቸው፤ ሰሓቦቼ ስሄዱ (ከፈተና) ለህዝቦቼ የተቀጠሩት ነገር ይመጣባቸዋል፡፡›[1]

እምነት (ዲን) ከመለኮታዊ ራእይ እንጂ አይወሰድም፡፡ ይህንንም ስል ቁርኣንና ሱናን ለማለት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿هُوَ ٱلَّذِي بَعَثَ فِي ٱلۡأُمِّيِّـۧنَ رَسُولٗا مِّنۡهُمۡ يَتۡلُواْ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمۡ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ﴾ [الجمعة: ٢]

እርሱ ያ በመሃይሞቹ ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርኣንን)**.** በነርሱ ላይ የሚያነብላቸው **(**ከማጋራት**)** የሚያጠራቸውም መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የኾነን መልክተኛ **(**ሙሐመድን**)** ከነሱው ውስጥ የላከ ነው፡፡ *(አል ጁሙዐ፡ 2)*

በሀይማኖት ዉስጥ ከሁለቱ ዉጪ እውቀትን መፈለግ ጅህሊና ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ትክክለኛው የወሕይ ግንዛቤ የሰሓቦች ግንዛቤ ነው፡፡ ስለዚህ እኛ ወሕይ ያመላከተንን፤ ሰሓቦች የተገበሩትንና በላጭ ትውሊድ የተስማሙበትን ነገር እንናገራለን፡፡

1 ሙስሊም በሐዲስ ቁጥር 2531 ዘግቦታል፡፡

# ክፍል አንድ

ኢስላም ብቸኛው የአላህ ሀይማኖት ነው፡፡ አላህ ከባሮቹ ጅንም ሆኑ ሰዎች ከሱ ሌላ አይቀበላቸውም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡፡

ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፡፡ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡ *(አሊ ዒምራን፡ 85)*

ኢስላም የሁሉም ነቢያቶች ሀይማኖት ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡

﴿وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ﴾ [الأنبياء: ٢٥]

ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም፡፡

አሁንም አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ كَمَآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ نُوحٖ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ مِنۢ بَعۡدِهِۦۚ وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَ وَٱلۡأَسۡبَاطِ وَعِيسَىٰ وَأَيُّوبَ وَيُونُسَ وَهَٰرُونَ وَسُلَيۡمَٰنَۚ وَءَاتَيۡنَا دَاوُۥدَ زَبُورٗا﴾

[النساء: ١٦٣ – ١٦٥]

አላህ ለነቢያችን ስለ ኑሕ፣ እብራሂም፣ እስሓቅ፣ ያዕቁብ፣ ዳውድ፣ ሱለይማን፣ አዩብ፣ ዩሱፍ፣ ሙሣ፣ሃሩን፣ ዘከሪያ፣ ያሕያ፣ ዒሣ፣ እልያስ፣ እስማዒል፣ የሰዐ፣ ዩኑስ እና ሉጥን ካወሳላቸው ቡኃላ እንዲህ አለ፡-

﴿أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ هَدَى ٱللَّهُۖ فَبِهُدَىٰهُمُ ٱقۡتَدِهۡ﴾ [الأنعام: ٩٠]

‹እነዚህ አላህ የመራቸው (ነቢያቶች) ናቸው፡፡ መመርያቸውን ተከተል፡፡› *(አል-አንኣም፡ 90)*

የነቢያቶች ዲን መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ይስማማል፤ በሁሉም ሳይሆን በአንዳንድ ቅርንጫፎች ላይ ግን ይለያያል፤ ስለዚህ ቅርንጫፎች ልለያዩ ይችላሉ፤ መሠረታዊ ነገሮች ላይ ግን አይለያዩም፡፡ አላህ (ሱወ) ለእስራኢል ልጆች ሙሣን እና ዒሣን መልክተኛ አድርጎ ልኮላቸዋል፡፡ እናም ዒሣ ላይ በወረደው እንጂል ሙሣ ላይ ከወረደው ተውራት የተወሰነውን ሽሯል፡፡

ሙሣ እና ዒሣ ለአንድ ህዝብ የተላኩ መልዕክተኞች ከመሆናቸውም ጋር አንዳንድ የዲን ቅርንጫፎቻቸው ልዩነት ካላቸው ታዲያ የተለያዩ ነቢያት የተላኩላቸው ሌሎች ህዝቦች ቅርንጫፎቻቸው ላይ እንዴት ልዩነት አይኖራቸውም?

ከዚያም ሸሪዓ ሆኖ ማዛባቶች እና ከሸሪዓው አመለካከት ወጣ ያሉ ጽንሰ አሳቦች የተቀላቀሉበት ቢሆን እንጂ መዝለቅ አልቻለም፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَإِنَّ مِنۡهُمۡ لَفَرِيقٗا يَلۡوُۥنَ أَلۡسِنَتَهُم بِٱلۡكِتَٰبِ لِتَحۡسَبُوهُ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَمَا هُوَ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَيَقُولُونَ هُوَ مِنۡ عِندِ ٱللَّهِ وَمَا هُوَ مِنۡ عِندِ ٱللَّهِ وَيَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلۡكَذِبَ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ﴾ [آل عمران: ٧٨]

ከእነሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲኾን ከመጽሐፉ መኾኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ፡፡ እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልኾነ ሲኾን «እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም» ይላሉ፡፡ እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡- ንግግሮችን ከስፍራው ያጠምማሉ፡፡ *(አን- ንሳእ፡ 46)*

እናም አብዛኛውን ሰው እና ሐቅን እንዳይገናኙ በመካከላቸው ጋርዷል፡፡ ይህም የምስተካከለው በአዲስ ነብይ ስለሆኔ አላህ ትክክለኛ እና ሐቅ የሆነውን ሀይማኖቱን በሙሐመድ ነብይነት ደገመው፡፡ እስልምናም ሆነ ትክክለኛ እምነት የለም የእርሱ (የሙሐመድ) እምነት ቢሆን እንጂ፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَن يَبۡتَغِ غَيۡرَ ٱلۡإِسۡلَٰمِ دِينٗا فَلَن يُقۡبَلَ مِنۡهُ وَهُوَ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ﴾ [آل عمران: ٨٥]

3|85| ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፡፡ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡

መልዕክታቸውንም ለሁሉም ህዝብ የሰው ልጅ እና ጋኔንን ጨምሮ  እንዲሁም ዐረቡንና ከዐረብ ውጪ ያሉትንም ሁሉ ያቀፈ አደረገ፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا كَآفَّةٗ لِّلنَّاسِ بَشِيرٗا وَنَذِيرٗا﴾ [سبأ: ٢٨]

‹‹ለሰው ልጆች በአጠቃላይ አብሳሪ እና አስጠንቃቂ አድርገን እንጂ አልላክንህም፤...›› *(አስ-ሰበእ፡ 28)*

ሙስሊም ከአቢ ሁረይራ የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፈዋል፡- ‹‹የሙሐመድ ነፍስ በእጁ ባለችው ይሁንብኝ! ከዚህ ህዝብ አይሁድም ይሁን ክርስትያን ስለ እኔ ከሰማ ቡኃላ እኔ የተላኩበትን ነገር ሳያምን ቢሞት ከእሳት ሰዎች ቢሆን እንጂ አይቀርም›› ብለዋል፡፡

አላህ (ሱወ) ቁርኣንን ከመለወጥ እና ከመበረዝ ጠብቋል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ﴾ [الحجر: ٩]

‹‹እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን›› *(አል ሒጅር፡ 9)*

# ክፍል ሁለት

እስላምን መተርጎም እና የአላህን ፍላጎትን መግለጽ ማንም አይችልም፤ አላህ በራሱ መጽሓፍ ውስጥ እና በላከው ነብይ ፈለግ (ሱና) ውስጥ ካልገለጸው በቀር፡፡ ከሰዎች መካከል ከነብዩ በላይ የተከበረ የለም፡፡ ይህም ከመሆኑ ጋር የጌታቸውን መልዕክት ከማድረስ ውጪ ሌላ ሚና የላቸውም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلرَّسُولُ بَلِّغۡ مَآ أُنزِلَ إِلَيۡكَ مِن رَّبِّكَ﴾ [المائدة: ٦٧]

‹‹አንተ መልዕክተኛው ሆይ! ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደውን አድርስ፤…›› *(አልማኢዳህ፡ 67)*

መልዕክተኛው (ሰዐወ) መልዕክቱን ከማድረስ በተጨማሪ ለሰዎች ግልጽ የማድረግ አላፊነትም አለባቸው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَا عَلَى ٱلرَّسُولِ إِلَّا ٱلۡبَلَٰغُ ٱلۡمُبِينُ﴾ [النور: ٥٤]

‹‹መልዕክተኛው ላይ ግልጽ የሆነ ማድረስ እንጂ ሌላ (ግዴታ) የለበትም፡፡›› *(አልኑር 54)*

ግልጽ ማድረግ ከአላህም ይጠበቃል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِذَا قَرَأۡنَٰهُ فَٱتَّبِعۡ قُرۡءَانَهُۥ ۝١٨ ثُمَّ إِنَّ عَلَيۡنَا بَيَانَهُۥ﴾ [القيامة: ١٨ – ١٩]

‹‹ባነበብነውም ጊዜ ንባቡን ተከተል፤ ከዚያም ማብራራቱ በእኛ ላይ ነው፡፡›› *(አልቅያማህ 18-19)*

ሱና ከአላህ ወደ ነብዩ የተላለፈ ራእይ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَا يَنطِقُ عَنِ ٱلۡهَوَىٰٓ ۝٣ إِنۡ هُوَ إِلَّا وَحۡيٞ يُوحَىٰ﴾ [النجم: ٣ – ٤]

‹‹(ሙሐመድ) ከስሜት አይናገርም፤ እሱም የምተላለፍ ራእይ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡›› *(አልነጅም፡ 3፣4)*

ነብዩ አንድን ጥያቄ በተጠየቁ ጊዜ ያንን ጥያቄ አስመልክቶ ከጌታቸው ቀደም ብሎ መልስ ደርሷቸው ከሆነ ይመልሳሉ፡፡ ካልሆነ ግን ራእይ እስከወርድላቸው ድረስ ይጠብቃሉ፡፡

ነብዩን ለመረዳት ይበልጥ ቅርብ የሆኑት ሰሓቦቻቸው ናቸው፡፡ ቁርኣንን እነርሱ

በተረዱት መልኩ መረዳት ማስረጃ ነው፡፡ አንድ ሰው ከአላህ ውጪ ዲኑን አስመልክቶ ህግ ማውጣት፣ ሐራም እና ሐላል ማድረግ ይችላል ያለ ሰው በእርግጥም የአላህን ውሳኔ አስመልክቶ ለአላህ ተጋሪን አድርጓል፡፡ ይህ ደግሞ ሽርክ እና ኩፍር መሆኑን ሁሉም የምስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡

አላህ (ሱወ) መጽሓፉን ስያወርድ ለንግግሩ እርሱ የምፈልገው ትርጉም ያለው ቢሆን እንጂ አላወረደም፡፡ የእርሱን ፍላጎት ደግሞ እርሱ ካልሆነ በቀር ወይም እርሱ የፈቀደለት አካል ካልሆነ በቀር መግለጽ አይችልም፡፡

ቁርኣንን በትኩረት የተመለከተ ሰው በሁለት መስፈርቶች ከቁርኣን ትምህርት መውሰድ ይችላል፡፡ እነርሱም፡-

አንደኛው፡ ከዐረቢኛ ቋንቋና የንግግር ዘይቤ መውጣት የለበትም፡፡

ሁለተኛው፡ በቁርኣን ውስጥ ያለውን ትክክለኛ እና ግልጽ የሆነውን ትርጉም መቃረን የለበትም፡፡

ማንኛውም ወደ አላህ የምናስጠጋው ነገር ሁሉ የአላህ አይደለም፡፡ አይሁዶች እና ክርስትያኖች የመጽሓፉን መልዕክት መረዳትን አስመልክቶ ድንበር በማለፍ፣ ቃላቶቹን በማጣመም እና በመሳሰሉት ድንበር በማለፍ ጠመዋል፡፡ እነርሱን አስመልክቶ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَإِنَّ مِنۡهُمۡ لَفَرِيقٗا يَلۡوُۥنَ أَلۡسِنَتَهُم بِٱلۡكِتَٰبِ لِتَحۡسَبُوهُ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَمَا هُوَ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَيَقُولُونَ هُوَ مِنۡ عِندِ ٱللَّهِ وَمَا هُوَ مِنۡ عِندِ ٱللَّهِ وَيَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلۡكَذِبَ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ﴾ [آل عمران: ٧٨]

‹‹ከእነርሱም እርሱ ከመጽሓፉ ያልሆነ ሲሆን ከመጽሓፉ መሆኑን እንድታስቡ በመጽሓፉ ምላሶቻቸውን የምያጣምሙ ክፍሎች አሉ፤ እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልሆነ ሲሆን እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም ይላሉ፤ እነርሱ የሚያውቁም ሲሆኑ በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ፡፡ *(ኣሊ እምራን 78)* በሌላ ሳይሆን ‹‹ምላሶቻቸውን በመጽሓፉ ያጣምማሉ›› አለ፡፡

ደግሞም ከመጽሓፉ ጋር በጣም ስለምቀራረብ ‹‹ከመጽሓፉ መሆኑን እንድታስቡ›› አለ፡፡ ይህ እንግዲህ ሰዎችን ለማጥመም ካላቸው ፍላጎት የተነሳ የሚያደርጉት ነገር ነው፡፡

# ክፍል ሦስት

የአላህ ሐቅ፡ የአላህ ሐቅ ማለት በሁሉም የዒባዳ ዓይነቶች እሱን በአምልኮ መነጠል ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَإِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَاحِدٌ ۖ لَّا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الرَّحْمَٰنُ الرَّحِيمُ﴾ [البقرة: ١٦٣]

‹‹አምላካችሁም አንድ አምላክ ነው፤ ከእርሱ ውጪ በሐቅ የምመለክ አምላክ የለም፤ እጅግ በጣም ሩሕሩሕ አዛኝ ነው፡፡›› *(አለ በቀራህ 163)*

በቀልብ፣ በምላስ እና በአካል በምሰሩ *ሥራዎች* ከእርሱ ጋር ምንንም ያለማጋራት ነው፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا﴾ [النساء: ٣٦]

‹‹አላህን አምልኩ በእርሱ ምንንም አታጋሩ›› *(አል ንሳእ 36)*

ትልቁ ሽርክ ለሰው ልጅ ከመልካም *ሥራው* ምንንም አያስተርፍለትም፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلَقَدْ أُوحِيَ إِلَيْكَ وَإِلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكَ لَئِنْ أَشْرَكْتَ لَيَحْبَطَنَّ عَمَلُكَ وَلَتَكُونَنَّ مِنَ الْخَاسِرِينَ﴾ [الزمر: ٦٥]

‹‹በእርግጥም ወደ አንተ እና ካንተ በፊት ወደ ነበሩት **(**መልዕክተኞች**)** ብ*ታጋራ ሥራ*ህ ይጠፋል፤ ከከሳሪዎችም ትሆናለህ **(**የምል ራእይ**)** ተላልፏል፡፡›› *(አልዙመር፡ 65)*

ይህ የተባለው ለነቢያችን ሙሐመድ (ሰዐወ) ከሆነ፡ ከእሳቸው ውጪ ያሉ ሰዎችስ ምን ይባሉ ይሆን?

አላህ በተውበት ቢሆን እንጂ ለባሪያው ሽርክን አይምርም፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّ اللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَاءُ﴾ [النساء: ٤٨]

‹‹አላህ በእርሱ መጋራትን አይምርም፤ ከዚህ ውጪ ያለውን ግን ለፈለገው ሰው ይምራል፡፡›› *(አል-ንሳእ፡ 48)*

በሙሐመድ ምዕራፍ ቁጥር 34 ላይም፡-

﴿إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ ثُمَّ مَاتُواْ وَهُمۡ كُفَّارٞ فَلَن يَغۡفِرَ ٱللَّهُ لَهُمۡ﴾ [محمد: ٣٤]

‹‹እነዚያ የካዱት ከአላህ መንገድም (ሰዎችን) የመለሱ ከዚያም (ሳይቶብቱ) ከሃዲ ሆነው የሞቱ አላህ ፈጽሞ አይምራቸውም፡፡››

ክህደት ላይ እያለ የሞተ ሰው እርሱ የእሳት ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَن يَرۡتَدِدۡ مِنكُمۡ عَن دِينِهِۦ فَيَمُتۡ وَهُوَ كَافِرٞ فَأُوْلَٰٓئِكَ حَبِطَتۡ أَعۡمَٰلُهُمۡ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ﴾ [البقرة: ٢١٧]

‹‹ከእናንተ ውስጥ ከሃይማኖቱ የሚመለስና እርሱም ከሃዲ ሆኖ የሚሞት ሰው እነዚያ (መልካም) ሥራቸው በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ሀገር ተበላሹ፡፡ እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፡፡ እነርሱ በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡›› *(አልበቀራህ፡ 217)*

﴿إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَمَاتُواْ وَهُمۡ كُفَّارٌ أُوْلَٰٓئِكَ عَلَيۡهِمۡ لَعۡنَةُ ٱللَّهِ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ وَٱلنَّاسِ أَجۡمَعِينَ﴾ [البقرة: ١٦١]

‹‹እነዚያ የካዱ እነርሱ ከሃዲ ሆነውም የሞቱ እነዚያ በእነርሱ ላይ የአላህ፣ የመላእኮች እና የሁሉም ሰዎች እርግማን አለባቸው፡፡›› *(አልበቀራህ፡ 161)*

አንዳንድ ጊዜ በአላህ የካዴ ሰው በህይወት እያለ ለሰዎች ጠቃሚ ልሆን ይችላል፡፡ ይህ አላህ (ሱወ) በተፈጥሮ ፀሓይን፣ ጨረቃን፣ ንፋስን፣ ዳመናን እና ሌሎች ለሰዎች ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን እንዳገራው ሁሉ እሄንን ሰውዬም አግርቶት ነው፡፡ ክህደት በተፈጥሮ ባህሪ ከሃዲ በመሆን ሳይሆን በአላህ በመካድ የሚገኝ ነገር ነውና፡፡ ቅጣትም የሚመጣው የተፈጥሮ ባህሪን በመካድ ሳይሆን የአላህን ሐቅ በመካድ ነው፡፡

❁ ❁ ❁

# ክፍል አራት

እምነት እና ክህደት፡ ሁለት የተለያዩ ስሞች እና ውሳኔዎች ሲሆኑ ከአላህ ውጪ ማንም ልወስናቸው የማይችላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ከአላህ በሆነ ግልጽ ማስረጃ ቢሆን እንጂ ማንም ከሃዲ ተደርጎ ልፈረጅ አይችልም፡፡ ሰዎች በምድር ላይ በሁለት ጎራ ቢቻ ይከፈላሉ፡፡ በሦስት መከፈል አይችሉም፡፡ እነሱም፡- ከሃዲ እና አማኝ ናቸው፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿هُوَ ٱلَّذِي خَلَقَكُمْ فَمِنكُمْ كَافِرٌ وَمِنكُم مُّؤْمِنٌ ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ﴾ [التغابن: ٢]

‹‹እርሱ ያ የፈጠራችሁ ነው፡፡ ከእናንተም ከሃዲ አለ፡፡ ከእናንተም አማኝ አለ፡፡›› *(አት-ተጋቡን፡ 2)*

ሁለቱን አስመልክቶ ውሳኔ የምሰጠው አላህ (ሱወ) በቁርኣን ውስጥ በገለጸው እና ነቢዩ (ሰዐወ) በሐዲሳቸው በገለጹት መልክ ብቻ ነው፡፡

ሙናፊቆችን በተመለከተ ደግሞ እነርሱ ከሁለቱ አንዱ ናቸው፡፡ ወይ ክህደቱን ደብቆ ማመኑን ብቻ ግልጽ ያደረገ ከሃዲ ነው፡፡ ልክ በአላህ፣ በቁርኣን እና በመልዕክተኛው ማመኑን ግልጽ አድርጎ በውስጡ ግን እንዳስተባበለ ሰው፡፡ ይህ ደግሞ ትልቁ ንፋቅ ነው፡፡

ወይም ደግሞ ሙስሊሞች ሆነው ወንጀልን ደብቀው ዒባዳቸውን ግልጽ ያደረጉ ናቸው፡፡ ቃል ከዳን ጠባቂ መሆኑን ግልጽ አድርጎ በውስጡ ግን ቃል ክዳኑን ማፍረስ እንዳሰበ ሰው፣ በንግግሩ እውነተኛ የሚመስል እና ውስጡ ግን የዚህ ተቃራኒ የሆነ ሰው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ትንሹ ንፋቅ ይባላል፡፡ ሙናፊቅ ጋር፡ ላይ ላዩን እንደ ሙስሊም እንኗኗረዋለን፡፡

አንድ ሙስሊም በመሠረቱ ደሙም ሆነ ሐብቱ የተከበረ ነው፡፡ የካፊር ደግሞ ከሙስሊሞች ጋር የሚዋጋ ከሆኔ የተፈቀደ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሁሉም ካፊር ማለት አይደለም፡፡ አንድ ካፊር በቃል ክዳኑ እና ከሙስሊሞች በተሰጠው ከለላ ምክንያት ህይወቱ እና ሐብቱ አይነካም፡፡ አንድ አማኝ ደግሞ በወንጀሉ ምክንያት ለምሳሌ ሰውን ከገደለ ወይም ካገባ ቡኃላ ዝሙት ብሰራ ይገደላል፡፡

- አላህ እና መልክተኛው ከሃዲ ካደረጉት ሰው በቀር ማንም ከሃዲ ተደርጎ ልፈረጅ አይችልም፡፡

ለምሳሌ፡ አላህን ወይንም መልክተኛውን ካስተባበለ ወይም ካላገጠባቸው አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

‹‹በአላህ፣ በአንቀፆቹ በመልክተኛው ታላግጡ ነበራችሁን? በላቸው፡፡ አታመካኙ ከእምነታችሁ ቡኃላ በእርግጥ ካዳችሁ፡፡ ከእናንተ አንዷን ጭፍራ ብንምር ሐጢሃተኞች በመሆናቸው (ሌላኛዋን) አንዷን ጭፍራ እንቀጣለን፡፡›› *(አት-ተውባ፡ 65፡ 66)*

- አላህን እና መልዕክተኛውን መታዘዝ እንቢ ብሎ ከተቃወማቸው
- ከእስላም ህግጋቶች በግልጽ የምታወቁትን መቀበል እንቢ ካለ
- በአላህ ላይ ከዋሼ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

‹‹ውሸትን የምቀጣጥፉት እነዚያ በአላህ አንቀጾች የማያምኑት ናቸው፡፡ እነዚያም ውሸታሞቹ እነርሱው ናቸው፡፡›› *(አን-ነሕል፡ 105)*

አሁንም እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَنۡ أَظۡلَمُ مِمَّنِ ٱفۡتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَوۡ كَذَّبَ بِٱلۡحَقِّ لَمَّا جَآءَهُۥٓۚ أَلَيۡسَ فِي جَهَنَّمَ مَثۡوًى لِّلۡكَٰفِرِينَ ﴾ [العنكبوت: ٦٨]

‹‹በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጠፈ ወይም እውነትን በመጣለት ጊዜ ካስተባበለ ሰው በላይ በዳይ ማነው?›› በገሃነም ውስጥ ለከሃዲዎች መኖሪያ የለምን?›› *(አልአንከቡት፡68)* እዚህ ጋ በደል በክህደት ተተረጎመ፡፡

- አምልኮን ከአላህ ውጪ ላለ ነገር ያደረገ ከሆነ፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَن يَدۡعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ لَا بُرۡهَٰنَ لَهُۥ بِهِۦ فَإِنَّمَا حِسَابُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦٓۚ إِنَّهُۥ لَا يُفۡلِحُ ٱلۡكَٰفِرُونَ ﴾ [المؤمنون: ١١٧]

‹‹ለእርሱ ማስረጃ የሌለውን ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የተጣራ ሰው የእርሱ ሕሳብ ጌታው ዘንድ ነው፡፡ እነሆ ከሃዲዎች የምፈልጉትን ነገር አግኝተው ከምፈሩት ነገር ነፃ አይሆኑም፡፡›› *(አልሙእሚኑን፡ 117)*

ይህ ሰው ከአላህ ውጪ ያለን ነገር ብቻ ቢያመልክ ወይም ከአላህ ውጪ ያለን ነገር በእርሱ እና በአላህ መካከል ጣልቃ ብያስገባም ክህደት ነው፡፡

- እና ውሳኔን መስጠት እንደዚሁም ሐላል እና ሐራም ማድረግን የመሳሰሉ ናቸው፡፡ ህግ ማውጣትን እና ዳኝነት መስጠትን አላህ አምልኮ ብሎ ጠርቷቸዋል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنِ ٱلۡحُكۡمُ إِلَّا لِلَّهِۚ أَمَرَ أَلَّا تَعۡبُدُوٓاْ إِلَّآ إِيَّاهُۚ﴾ [يوسف: ٤٠]

‹‹ፍርዱ የአላህ እንጂ የሌላ አይደለም፤ እርሱን እንጂ ሌላን እንዳታመልኩ አዟል፡፡›› *(ዩሱፍ፡ 40)*

- ከአላህ ውጪ ላሌ ነገር የሩቅ ምስጥርን ካረጋገጤ፡ ለምሳሌ፡- ድግምት እና ኮከብ ቆጠራን የመሳሰሉትን አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

‹‹ከአላህ ውጪ በሰማያት ውስጥ እና በምድር ያሉት የሩቅ ምስጥርን አያውቁም በላቸው፡፡›› *(አልነምል ፡65)*

- መፍጠርን እና ማስተናበርን መግደል እና ማዳንን የሞገተ ከሆነ፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿أَمْ جَعَلُوا۟ لِلَّهِ شُرَكَآءَ خَلَقُوا۟ كَخَلْقِهِۦ فَتَشَٰبَهَ ٱلْخَلْقُ عَلَيْهِمْ ۚ قُلِ ٱللَّهُ خَٰلِقُ كُلِّ شَىْءٍ وَهُوَ ٱلْوَٰحِدُ ٱلْقَهَّٰرُ﴾ [الرعد: ١٦]

‹‹... ወይስ ለአላህ እንደርሱ አፈጣጠር የፈጠሩን ተጋሪዎች አደረጉለትና ፍጥረቱ በእነርሱ ላይ ተመሳሰለባቸውን? አላህ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው፤ እርሱም አንዱ አሸናፊው ነው›› በል፡፡ *(አልረዕድ፡ 16)*

- ከሙእሚኖች ውጪ ካፍሮችን ወዳጅ እና ረዳት አድርጎ የያዜ ሰውም ከዚሁ ይመደባል፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَن يَتَوَلَّهُم مِّنكُمْ فَإِنَّهُۥ مِنْهُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلظَّٰلِمِينَ﴾ [المائدة: ٥١]

‹‹...ከእናንተ ወዳጅ ያደረጋቸው ሰው እርሱ ከእነርሱ ነው፡፡›› *(አልማኢዳ፡ 51)*

- እስላምን ለማወቅ እድል ካገኘ ቡኃላ መማር ትቶ በራሱ ምርጫ ከእሱ የዞረ ሰው መሃይም እንኳ ቢሆን ካፍር ይባላል፤ ምክኒያቱም መሃይምነቱን ማስወገድ እየቻለ ያላስወገደ ሰው ነውና፡፡ ለዚህም ነው አላህ (ሱወ) ሙሽርኮችን አስመልክቶ እንዲህ በማለት የተናገረው፡-

‹‹... በእውነቱ አብዛኞቻቸው እውነቱን አያውቁም፤ ስለዚህ እነሱ እንቢተኞች ናቸው፡፡›› (አል አንቢያእ፡ 24)

መሃይምነታቸው በራሳቸው ምርጫ መሆኑን አላህ ገለጸ፡፡

እንዲህም ይላል፡-

﴿مَا خَلَقْنَا ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَآ إِلَّا بِٱلْحَقِّ وَأَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ عَمَّآ أُنذِرُوا۟ مُعْرِضُونَ﴾ [الأحقاف: ٣]

‹‹እነዚያ የካዱት ከተስጠነቀቁበት ነገር (ትተው) የምዞሩ ናቸው፡፡›› *(አልአሕቃፍ፡ 3)*

አንድ ሰው ሐቅን በሰማ ጊዜ እምቢ ቢሎ በመዞሩ ምክንያት የተወሰኑ ሐቆችን

ሳያውቅ ብቀር ይህ ያለማወቁ ምክንያት ልሆንለት አይችልም፤ ይህ አብዛኛው ህዝብ የተሳሳተበት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ከሐቅ የተወሰነውን ከሰሙ ቡኃላ በዝርዝር ሳያውቁ ከሐቅ ይዞራሉ፡፡

ለተፈጥሯዊ እና ሸርዓዊ ማስረጃዎች ቦታ ያለመስጠት የብዙ ከሃዲያን ባህሪ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَكَأَيِّن مِّنْ ءَايَةٍ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ يَمُرُّونَ عَلَيْهَا وَهُمْ عَنْهَا مُعْرِضُونَ﴾ [يوسف: ١٠٥]

‹‹ከተዓምራት ስንትና ስንት ናቸው በሰማያት ውስጥ እና በምድርም ያሉ በእሷ አጠገብ እነርሱም ከእሷ (የማያስተነትኑ ሲሆኑ) ዟሪዎች ሆነው ያልፋሉ፡፡›› *(ዩሱፍ፡ 105)*

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلَوِ ٱتَّبَعَ ٱلْحَقُّ أَهْوَآءَهُمْ لَفَسَدَتِ ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلْأَرْضُ وَمَن فِيهِنَّ ۚ بَلْ أَتَيْنَٰهُم بِذِكْرِهِمْ فَهُمْ عَن ذِكْرِهِم مُّعْرِضُونَ﴾ [المؤمنون: ٧١]

‹‹ይልቁንም ክብራቸው ያለበትን *(ቁርዓንን)* አመጣንላቸው፤ እነርሱም ከክብራቸው ዘንጊዎች ናቸው፡፡›› *(አልሙእሚኑን፡ 71)*

አነስተኛ እውቀትን ይዞ ከሐቅ መዞር ሰዎች አንዳቸው ከአንዳቸው ያላቸውን ሐቅ እንዳይጠብቁ ምክኒያት ሊሆን አይችልም፡፡ ታዲያ የአላህን ሐቅ ላለመጠበቅ እንዴት ምክኒያት ሊሆን ይችላል?

አዕምሮ የቁርኣን አንቀጾች ጋር ቆም ብሎ ካላስተነተነ ቁርኣን የወረደበት ምስጥር (ዓላማ) እርሱ ባደረገው ፊጥነት ልክ ያመልጠዋል፡፡ ይህ ሰው የቁርኣን ማስረጃዎቹ ግልጽ እና ታላቅ ተጽዕኖ ማሳደር የምችሉ የሚታዩ ተዓምራቶች እንኳ ቢሆኑ መጠቀም አይችልም፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَجَعَلْنَا ٱلسَّمَآءَ سَقْفًا مَّحْفُوظًا ۖ وَهُمْ عَنْ ءَايَٰتِهَا مُعْرِضُونَ﴾ [الأنبياء: ٣٢]

‹‹ሰማይንም (ከመውደቅ) የተጠበቀ ጣራ አደረግን፡፡ እነሱም ከተዓምራቷ ዘንጊዎች ናቸው፡፡›› *(አልአንቢየእ፡ 32)*

አንድ ሰው ሐቅ የሆኑ ዝርዝር ነገሮችን ማወቅ ትቶ ጀርባውን በመስጠቱ ከተጠያቂነት የሚያድነው መስሎት ይሳሳታል፡፡

አንድ ሰው ከሐቅ የምዞሪባቸው ምክኒያቶች፡ ከኩራት ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም በመሳለቅ ወይም በዚህች ዓለም ላይ ለመዝናናት አስቦ ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህም ነው አንድ ችግር በደረሰበት ጊዜ ኩራቱ የምወገደው፤ መጣቀሚያውንም የሚያጣው፡ እናም ሐቁን አይቶ ወደ ሐቁ የምመለሰው፡፡

# ክፍል አምስት

ኢማን/እምነት/፡ ንግግር ነው፤ ሥራም ነው፤ በቀልብም የሚታመን ነገር ነው፡፡ እነዚህ ሦስቱም ኢማን ናቸው፡፡ መግሪብ ሦስት ረከዓ ከመሆኑ ጋር አንድ ረከዓ ብጎድልበት መግሪብ እንደማይባል ሁሉ ከኢማንም አንዱ ብጎድል ኢማን አይባልም፡፡

ከእነዚህ ሦስቱ አንዱ በመጉደሉ ምክንያት ኢማን መታጣቱ የነቢያችን ሙሐመድ (ሰዐወ) የሸሪዓ ህግ ከሌሎች የተለየበት ተጨባጭ ነው፡፡ የቀልብ እምነት ሲባል ለሰዎች ጥሩን ነገር መመኘት ልባችንን ከጥላቻ ነፃ ማድረግ ለማለት አይደለም፡፡ ምክኒያቱም ይህ ፈጣሪ መኖሩን የማያምኑ ሰዎችን ጨምሮ አብዛኛው ሰው የሚስማማበት ጉዳይ ነውና፡፡ ነገር ግን ለማለት የተፈለገው የቀልብ ንግግርን  እና ሥራውን ነው፡፡

የቀልብ ንግግር ማለት ከአላህ ውጪ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም፤ ሙሐመድ (ሰዐወ) የአላህ መልዕክተኛ ናቸው፤ ከጌታቸው ይዘው የመጡትም ነገር ሐቅ ነው ብሎ ማመን ነው፡፡

የቀልብ ሥራ አላህን መውደድ፣ የእርሱን ነብይ መውደድ፣ እስልምናን መውደድ፣ አላህ እና መልዕክተኛው የሚወዱትን ነገር መውደድ፣ አምልኮን ለእርሱ ብቻ ማድረግ፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ንግግር ሲባል መልካም ተብለው በሚታወቁት ንግግሮች ላይ ብቻ አይወሰንም፡፡ ለምሳሌ፡- እውነት መናገር፣ ለወላጆች ለስለስ ያለን ንግግር መናገር፣ ሠላምታን መስጤት፣ መንገድ የጠፋውን መንገድ ማመላከት፣ ወዘተ፡፡ ይህንን አላህ መኖሩን የካዱ ሰዎች እና ከሐዲዎችን ጨምሮ ሁሉም ሰው ይወደዋል፡፡ ለማለት የተፈለገው ነብዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) የተላኩበትን ሲሆን ከእነዚህም መካከል ዋናው እና የመጀመሪያው ከአላህ ውጪ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም፤ ሙሐመድም የአላህ ባሪያ እና መልዕክተኛው መሆናቸውን መመስከር ነው፤ እንደዚሁም አላህን ማጥራት እና እርሱን ማላቅ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሥራም ሲባል በሰዎች ዘንድ የታወቁ መልካም ሥራዎች ላይ ብቻ አይወሰንም፡፡ ለምሳሌ፡- ለወላጆች መልካም ማድረግ፣ ሰዎችን የሚያስቸግሩ ነገሮችን ከመንገድ ማስወገድ፣ ድሃን ማብላት፣ የተበደለን መርዳት፣ እንግዳን ማክበር የመሳሰሉትን አይደለም፤ ምክኒያቱም ይህንን ያላመኑ ሰዎችም ይስማሙበታልና፡፡

ሥራ ሲባል ለማለት የተፈለገው፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) እንዲያደርሱት የታዘዙትን ሰላት፣ ዘካ፣ ፆም ሐጅ የመሳሰሉትን ለማለት ነው፡፡

መለኮታዊ መልዕክቶች እና የሰው ልጅ ተፈጥሮ ከሚስማሙባቸው መልካም ሥራዎች መካከል፡- መልካም ነገሮችን ለሰው ልጅ መውደድ፣ እውነት መናገር፣ ለወላጆች መልካም ማድረግ፣ ሰዎችን የሚያስቸግሩ ነገሮችን ከመንገድ ማስወገድ፣ ድሃን ማብላት፣ የመሳሰሉት ለአላህ ተብለው በተሰሩ ጊዜ ኢማንን ይጨምራሉ፡፡ የእነዚህ ሥራዎች መታጣት ግን ኢማን የለም ማለትን አይሰጥም፤ እንደዚያውም የእነሱ መኖርም ኢማን አለ አያስብልም፡፡ የእነዚህ ሥራዎች መኖር የሚያረጋግጠው የሰው ልጆች የተፈጠሩባቸው ስብእናዎች በትክክል መኖራቸውን እና አለመለወጣቸውን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ስብእና ደግሞ ሐቅን ለመቀበል ከየትኛውም በላይ ቅርብ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فِطۡرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِي فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيۡهَا﴾ [الروم: ٣٠]

‹‹የአላህን ፊጥረት ያቺን አላህ ሰዎችን በእርሷ የፈጠረውን (እምነት/እስላምን) ያዟት፡፡›› *(አልሩም፡ 30)*

ኢማን፡ ይጨምራል፤ ይቀንሳል፤ ይጠፋል፡፡ አላህን በመታዘዝ ይጨምራል፤ በወንጀል ይቀንሳል፤ ሙሉ በሙሉ መጥፋት የሚችለው ግን በክህደት ወይም በጥሪጣሬ ብቻ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّمَا ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتۡ قُلُوبُهُمۡ وَإِذَا تُلِيَتۡ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتۡهُمۡ إِيمَٰنٗا﴾ [الأنفال: ٢]

‹‹ፍፁም አማኞች እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት በእነሱ ላይ አንቀጾቹ በተነበቡ ጊዜ ኢማን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው፡፡›› *(አል አንፋል፡ 2)*

﴿وَيَزۡدَادَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِيمَٰنٗا﴾ [المدثر: ٣١]

‹‹… እነዚያ ያመኑት እምነትን እንድጨምሩ …›› *(አልሙደስር ፡ 31)*

አሁንም እንዲህ ይላል፡-

﴿هُوَ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ ٱلسَّكِينَةَ فِي قُلُوبِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ لِيَزۡدَادُوٓاْ إِيمَٰنٗا مَّعَ إِيمَٰنِهِمۡ﴾ [الفتح: ٤]

‹‹እርሱ ያ በአማኞች ልብ ውስጥ ከእምነታቸው ጋር እምነትን እንድጨምሩ መረጋጋትን ያወረደው ነው፡፡›› *(አልፈትሕ፡ 4)*

ኢማን ከክህደት ቡኃላ በሚከተሉት ነገሮች ውጪ ልኖር አይችልም፡፡ እነርሱም፡

- በቀልብ ማመን፡ ይህም የቀልብ ንግግር ሲሆን እሱም በነብዩ (ሰዐወ) ላይ የወረደውን መልዕክት አምኖ መቀበል ነው፡፡ ሌለኛው ደግሞ የቀልብ ሥራ ነው፡፡

እሱም፡ አላህ እና መልዕክተኛውን መውደድ እንደዚሁም አላህ እና መልዕክተኛው የሚወዷቸውን ነገሮች መውደድ ናቸው፡፡

- በሚላስ መናገር
- በአካል መስራት ናቸው፡፡

በልቡ አምኖ በሚላሱ መናገር እየቻለ ያልተናገረ ሰው አምኗል አይባልም፡፡

በልቡ አምኖ በሚላሱም ተናግሮ ነግር ግን የነብያችን ሙሐመድ ሸሪዓ መገለጫ የሆነን ነገር መስራት እየቻለ ያልሰራ ሰው አምኗል አይባልም፡፡

መናገር እና መስራት እየፈለገ ያልቻለ ሰውን አስመልክቶ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَا﴾ [البقرة: ٢٨٦]

‹‹አላህ አንድን ነፍስ ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፡፡›› *(አልበቀራህ፡ 286)*

‹‹አላህ አንድን ነፍስ ከሰጣት ነገር በላይ አያስገድዳትም፡፡›› *(አጥ-ጠላቅ፡ 7)*

አንድ ሙስሊም በንግግርም ይሁን በሥራ ወይም የቀልብ እምነቶችን አስመልክቶ ኢማኑን የሚያጠፋበትን ነገር ቢሰራ ኢማኑ ሙሉ በሙሉ ይጠፋል፡፡ ምክንያቱም ኢማን የሚባሉት እነዚህ ሦስቱ (ንግግር፣ ተግባር እና የቀልብ እምነት) ናቸው፡፡ ሦስቱ ረከዓዎች መግሪብ እንደሚባሉት ሁሉ አንድ ሰጋጅ ሁለቱን ረከዓዎች በትክክል ሰግዶ ከእነዚህ ሦስቱ ረከዓዎች በአንዱ ረከዓ ላይ ሰላቱን የሚያጠፋበትን ሥራ ብሰራ የመግሪብ ሰላቱ እንደሚጠፋበት ሁሉ የዚህ ሰው ኢማንም ይጠፋበታል፡፡ ይህ ያልነው ግን ኢማን አላህን በመታዘዝ ይጨምራል፤ ወንጀሉ ትልቅም ይሁን ትንሽ በወንጀል ይቀንሳል ካልነው ጋር አይጋጭም፡፡ የዚህ ምሳሌ፡- ሰላትን ከሚያጠፉ ነገሮች መካከል አንዱን የሰራ ሰው ሰላቱ ይበላሻል፡፡ እንደዚሁም ሰላትን የማያጠፉ ነገር ግን ሰዋቡን የሚቀንሱ ነገሮችን የሰራ ሰው ከሰላቱ የሚያገኘው ሰዋብ ይቀንሳል እንጂ ሰላቱ አጥጠፋበትም፡፡

የሰላትን ሰዋብ ከፍ የሚያደርጉ ነገሮችን የሰራ ሰው ለምሳሌ፡ ቅራት ማስረዘም፣ ሰላት ውስጥ ለአላህ መተናነስ የመሳሰሉትን የሰራ ሰው ሰዋቡ እንደሚጨምር ሁሉ ኢማንም የዚህ ባህሪ አለው፡፡

አላህ ወይም መልዕክተኛው ኢማንን ያጠፋሉ ካሉዋቸው ነገሮች ውጪ ኢማንን የሚያጠፋ ነገር የለም፡፡ ሰላትም እንደዚያው ነው፡፡

# ክፍል ስድስት

ለአላህ የላቁ ባህሪያቶች እና ስሞች አሉት፡፡ ከእርሱ በላይ ስለ እርሱ የሚያውቅ የለም፡፡ እርሱ በቁርኣን እና በመልዕክተኛው ሐዲስ ውስጥ ከራሱ ውድቅ ያደረጋቸውን ነገሮች እኛም ውድቅ እናደርጋለን፡፡ ለራሱ ያረጋገጣቸውንም ነገሮች እናረጋግጥለታለን፡፡ ባጠቃላይ ማናቸውንም ጎደሎ ባህሪያቶችን ከእርሱ ውድቅ እናደርጋለን፡፡ የትኛውንም የሙሉዕነት ባህሪን አንድ በአንድ እናረጋግጥለታለን፡፡ ይህንን ስናረጋግጥ ግን አኳኋኑን ለመግለጽ ሳንሞክር፣ ከሌላ ነገር ጋር ሳናመሳስል እና ምን እንደሚመስልም በአዕምሮአችን ለመሳል ሳንሞክር ነው፡፡

በአንዳንድ ጎደሎ ባህሪያቶች በዝርዝር የገለጸው ሰው ካለ እኛም በዝርዝር ከእነዛ ጎደሎ ባህሪያቶች እናጠረዋለን፡፡ እርሱ ልጅን እና ሚስትን ከመያዝ ራሱን እንዳጠራው ሁሉ፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿بَدِيعُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ أَنَّىٰ يَكُونُ لَهُۥ وَلَدٞ وَلَمۡ تَكُن لَّهُۥ صَٰحِبَةٞۖ وَخَلَقَ كُلَّ شَيۡءٖۖ وَهُوَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٞ﴾ [الأنعام: ١٠١]

‹‹**….** ሚስት የሌለው ሲሆን ለእርሱ ልጅ እንዴት ይኖረዋል?›› *(አል-አንዓም: 101)*

በድጋሚ እንዲህ ይላል፡-

﴿لَمۡ يَلِدۡ وَلَمۡ يُولَدۡ﴾ [الإخلاص: ٣]

‹‹አልወለደም አልተወለደምም፡፡›› *(አልኢኽላስ: 3)*

አይሁዶች በስስት የገለጹትንም እንዲህ በማለት ከራሱ ውድቅ አድርጓል፡፡

﴿وَقَالَتِ ٱلۡيَهُودُ يَدُ ٱللَّهِ مَغۡلُولَةٌۚ غُلَّتۡ أَيۡدِيهِمۡ وَلُعِنُواْ بِمَا قَالُواْۘ بَلۡ يَدَاهُ مَبۡسُوطَتَانِ﴾ [المائدة: ٦٤]

‹‹አይሁዶችም የአላህ እጅ የታሰረች ናት አሉ፡፡ እጆቻቸው ይታሰሩ! ባሉትም ነገር ተረገሙ፡፡ እነርሱ እነደሚሉት ሳይሆን እጆቹ የተዘረጉ ናቸው፡፡›› *(አልማኢዳህ: 64)*

በቁርኣን እና በሐዲስ የተገለጸውን እንደ አመጣጡ እንቀበለዋለን፡፡ ከአላህ ስሞች እና ባህሪያቶች በቁርኣን በተገለጸው መልኩ ሳንጨምርበት እንቀበላለን፡፡ አላህ እርሱን የሚመስለው ነገር የለምና፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ﴾ [الشورى: ١١]

‹‹የሚመስለው ምንም ነገር የለም፡፡ እሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡›› *(አልሹራ፡ 11)*

የአላህን ባህሪያት ከሌላ ነገር ጋር ማነፃፀር አይፈቀድም፤ ምክንያቱም ያ የሚናነፃፀርበት ነገር ቅርንጫፍ እና ግንድ ይኖረዋል፡፡ አላህ ደግሞ አንድ ሲሆን አምሳያ የለውም፡፡ ስለዚህ ከእርሱ ጋር የሚስተካከል ቅርንጫፍም ይሁን ከእርሱ በላይ ሊሆን የሚችል ግንድ (መሠረታዊ ነገር) የለም፡፡ አንድ እና የሁሉም መጠጊያ የሆነ፣ ያልወለደ፣ የማይወለድ፣ እርሱንም የሚመስል አንድም ነገር የለሌ አምላክ ነው፡፡

አዕምሮ አላህ የፈጠራት መሣሪያ ስትሆን የምትሰማውን ነገር ካየችው ነገር ጋር ታነፃፅረለች፡፡ እናም አላህ ስለ ራሱ የተናገረውን  ትሰማና ከዚህ በፊት አላህን አይታው ስለማታውቅ ካየችው ነገር ጋር ይበልጥ ተቀራራቢ ሆኖ ካገኘችው ነገር ጋር ታነፃፅረዋለች፡፡ ሁሉም አዕምሮ ቀደም ብሎ ባየው ሁኔታ ያነፃፅራል፡፡ አኳኋኑንም ባየው ነገር ይቀርፃል፡፡ አላህ (ሱወ) በየትኛውም አዕምሮ ውስጥ አምሳያ የለውም፡፡ ውስጣችን ላይ የሚቀፈንን መጥፎ ምስል ለማስወገድ ብለን ከስሞቹ እና ከባህሪያቶቹ አንዱንም ትርጉም አልባ አናደርግም፤ ከስሞቹ ወይም ከባህሪያቶቹ አንዱን ውድቅ ብናደርግ ውድቅ በማድረጋችን የተሳሳተ ማነፃፀር ላይ ወደቅን ማለት ነው፡፡ እንደዚያውም (ከአላህ እና ከመልዕክተኛው (ሰዐወ)) የተላለፈውን ትክክለኛ ዘገባም አስተባበልን ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ማድረግ ያለብን መጥፎ ትርጉሙን ከአዕምሮአችን ማስወገድ ነው፡፡ አላህ ራሱን የሰየመበትን ስሞቹን እና ራሱን የገለጸበትን ባህሪያቶቹን እናረጋግጣለን፡፡ በዚህ ላይም እንወሰናለን፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡ وَلَا يُحِيطُونَ بِهِۦ عِلۡمٗا﴾ [طه: ١١٠]

‹‹ከበስተፊታቸው ያለውን  ከበስተኋላቸውም  ያለውን ሁሉ ያውቃል፡፡ በእውቀት እርሱን አያካብቡም፡፡›› *(ጣሃ፡ 110)*

﴿لَّا تُدۡرِكُهُ ٱلۡأَبۡصَٰرُ وَهُوَ يُدۡرِكُ ٱلۡأَبۡصَٰرَۖ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلۡخَبِيرُ﴾ [الأنعام: ١٠٣]

‹‹ዓይኖች አያዩትም፤ እርሱም ዓይኖችን ያያል፤ እርሱም ረቂቁ ውስጠ አዋቂው ነው፡፡›› *(አል አንዓም፡ 103)*

ታላቁ አላህ ከሰማይ በላይ ዐርሹ ላይ ተደላድሏል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿هُوَ ٱلۡأَوَّلُ وَٱلۡأٓخِرُ وَٱلظَّٰهِرُ وَٱلۡبَاطِنُۖ وَهُوَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٌ ٣ هُوَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ فِي

سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ ۚ يَعْلَمُ مَا يَلِجُ فِي ٱلْأَرْضِ وَمَا يَخْرُجُ مِنْهَا وَمَا يَنزِلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ وَمَا يَعْرُجُ فِيهَا ۖ وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴾ [الحديد: ٣ - ٤]

‹‹እርሱ የመጀመሪያው (ከእርሱ በፊት ምንም ያልነበረ)፣ መጨረሻውም (ከእርሱ ቡኃላ ምንም የማይኖር)፣ ግልጹም፣ ስውሩም ነው፤ እርሱም ሁሉንም ነገር አዋቂ ነው:: እርሱ ያ ሰማትን እና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ እና ከዚያም ዐርሹ ላይ የተደላደለ ነው፤ ምድር ውስጥ የሚገባን እና ከእርሷም የሚወጣን ሁሉ ያውቃል፤ ከሰማይ የሚወርደውን እና ወደ እርሷም የሚያርገውን ሁሉ ያውቃል፤ እርሱም በሆናችሁበት ቦታ ሁሉ ከእናንተ ጋር ነው፤ አላህም የሚትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነው::›› *(አልሐዲድ፡ 3፣4)*

በዛቱ መደላደሉን አረጋገጠ:: ሁሉንም ነገር ማወቁንም እንደዚያው:: ከባሮቹ ጋር አብሮ መሆኑንም ገልጿል:: አዎን እርሱ በእውቀቱ፣ በሰሚነቱና በተመልካችነቱ ከእነርሱ ጋር ነውና:: እንዲህም ይላል፡-

﴿ وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴾ [الحديد: ٤]

‹‹እርሱም በሆናችሁበት ቦታ ሁሉ ከእናንተ ጋር ነው፤...›› *(አልሐዲድ፡4)*

እርሱ በእርዳታው እና በእገዛው ከሚወዳቸው ባሮቹ ጋር ነው:: ለሙሳ እና ለሃሩን (ዐ.ሰ)፡-

﴿ قَالَ لَا تَخَافَآ ۖ إِنَّنِي مَعَكُمَآ أَسْمَعُ وَأَرَىٰ ﴾ [طه: ٤٦]

‹‹አትፍሩ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ እሰማለው እያለውኹም::›› (ጣሃ፡ 46)

አላህ (ሱ.ወ) ሁሉን ያቀፈ ፍላጎት አለው:: እርሱ ያሻው ነገር ይሆናል፤ ያላሻው ነገር ደግሞ አይሆንም:: እርሱ ለራሱ ባረጋገጠው ሁኔታ እናረጋግጥለታለን:: በአዕምሯቸው ላይ ተንተርሰው ጠለቅ ብለው ገብተው በመመራመር እና ሁለት የምጣረዙ ነገሮችን ለማስማማት እንደሚታትሩ ሰዎች ከተገለጸው በላይ ጠለቅ ብለን ገብተን አንመራመርም:: አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡

﴿ قَالَ كَذَٰلِكَ ٱللَّهُ يَفْعَلُ مَا يَشَآءُ ﴾ [آل عمران: ٤٠]

‹‹... **(መልአኩም)** እንደዚሁ አላህ ያሻውን ነገር ይሰራል አለ::›› *(ኣሊ እምራን፡ 40)*

﴿ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَفْعَلُ مَا يُرِيدُ ﴾ [البقرة: ٢٥٣]

‹‹ነገር ግን አላህ ያሻውን ይሰራል::›› *(አልበቀራህ፡ 253)*

﴿ ذُو ٱلْعَرْشِ ٱلْمَجِيدُ ﴿١٥﴾ فَعَّالٌ لِّمَا يُرِيدُ ﴾ [البروج: ١٥ - ١٦]

‹‹የዐርሹ ባለቤት የላቀው ነው፤ ያሻውን ሁሉ ሰሪ ነው፡፡›› *(አልቡሩጅ፡ 15፣ 16)*

ቁርኣን እና ሐዲስ ያረጋገጠውን እናረጋግጥለታለን፤ ከዚህ ውጪ ካለ ነገር ደግሞ እንታቀባለን፡፡ በቁርኣን እና በሐዲስ ባይገለጽም ከጎደሎ ባህሪያት አዕምሮ የማይቀበላቸውን ማልቀስ፣ ማዘን፣ መራብ የመሳሰሉትን ነገሮች ውድቅ እናደርጋለን፡፡

# ክፍል ሰባት

ቁርኣን ፊደሎቹም፣ አንቀጾቹም ሆኑ ምዕራፎቹ አላህ በተጨባጭ የተናገራቸው የአላህ ንግግሮች ናቸው፡፡ ‹‹የአላህ ቃል ትርጉም ነው ወይም ከአላህ የተተረከ ነው አንልም[1]፡፡›› ነገር ግን አላህ በፈለገው ጊዜ ከመናገር አይወገድም እንላለን፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَكَلَّمَ ٱللَّهُ مُوسَىٰ تَكۡلِيمٗا﴾ [النساء: ١٦٤]

‹‹አላህ ሙሳን ማናገርን አናገረው፡፡›› *(አል ንሳእ፡ 164)*

﴿وَلَمَّا جَآءَ مُوسَىٰ لِمِيقَٰتِنَا وَكَلَّمَهُۥ رَبُّهُۥ﴾ [الأعراف: ١٤٣]

‹‹ሙሳ ለቀጠሯችን በመጣና ጌታውም ባነጋገረው ጊዜ›› *(አል አዕራፍ፡ 143)*

- ንግግሩም እርሱ እንዳለው ነው፡-

﴿وَٱللَّهُ يَقُولُ ٱلۡحَقَّ﴾ [الأحزاب: ٤]

‹‹አላህም እውነትን ይናገራል፡፡›› *(አል አሕዛብ፡ 4)*

- የአላህን ንግግር ልቦች ይሸመድዳሉ፡፡አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿بَلۡ هُوَ ءَايَٰتُۢ بَيِّنَٰتٞ فِي صُدُورِ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡعِلۡمَ﴾ [العنكبوت: ٤٩]

‹‹ይልቁንም እርሱ (ቁርኣን) በእነዚያ እውቀትን በተሰጡት ሰዎች ልቦች ውስጥ (የጠለቀ) ግልጽ የሆኑ አንቀጾች ነው፡፡›› *(አል ዐንከቡት፡ 49)*

- በጆሮም የሚሰማ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَإِنۡ أَحَدٞ مِّنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ٱسۡتَجَارَكَ فَأَجِرۡهُ حَتَّىٰ يَسۡمَعَ كَلَٰمَ ٱللَّهِ﴾ [التوبة: ٦]

‹‹ከሙሽሪኮችም አንዱ ጥገኝነትን ብጠይቅህ የአላህን ንግግር ይሰማ ዘንድ ጥገኝነትን ስጠው፡፡›› *(አልተውባ፡ 6)*

1 ይህ አባባል የመጣበት ምክንያት የተወሰኑ ሰዎች፡ እኛ ጋ ያለው ቁርኣን የአላህ ቃል አይደለም፣ የሱ ትርጉም ነው እንጂ ይላሉ፡፡ ወይም ደግሞ ጂብሪል ከአላህ የተረከ ነው ይላሉ፡፡ ይህ መብራርያም የተጻፉት እነኚህ አባባሎች ትክክል ኣለ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

ቁርኣንን ለሰዎች የሚያደርሱት ነብዩ ቢሆኑም ይህ ቁርኣን የአላህ ቃል እንዳይሆን አያደርገውም፡፡

❁ በመጻፊያ ላይም የተጻፈ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡

﴿وَكِتَٰبٖ مَّسۡطُورٖ ٢ فِي رَقّٖ مَّنشُورٖ﴾ [الطور:٢ – ٣]

‹‹በተጻፈው መጽሐፍም፤ በተዘረጋ ብራና ላይ (በተጻፈው)›› *(አልጡር፡ 2፣3)*

አላህ እርሱ ዘንድ በተጠበቀው ሰሌዳ ውስጥ ጠብቆታል፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿بَلۡ هُوَ قُرۡءَانٞ مَّجِيدٞ ٢١ فِي لَوۡحٖ مَّحۡفُوظِۭ﴾ [البروج: ٢١ – ٢٢]

‹‹ይልቁንም እርሱ የከበረ ቁርኣን ነው፤ የተጠበቀ በሆነ ሰሌዳ ውስጥ ነው፡፡›› *(አልቡሩጅ፡ 21፣22)*

﴿وَإِنَّهُۥ فِيٓ أُمِّ ٱلۡكِتَٰبِ لَدَيۡنَا لَعَلِيٌّ حَكِيمٌ﴾ [الزخرف: ٤]

‹‹እርሱም በመጽሐፎቹ እናት ውስጥ እኛ ዘንድ በእርግጥ ከፍተኛ ጥበብ የተሞላ ነው፡፡›› *(አልዙኽሩፍ፡ 4)*

❁ የተጻፈ መሆኑ የአላህ ንግግር እንዳይሆን አያደርገውም፡፡ወረቀቱም ብዕሩም የተፈጠሩ ነገሮች ናቸው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلَوۡ نَزَّلۡنَا عَلَيۡكَ كِتَٰبٗا فِي قِرۡطَاسٖ﴾ [الأنعام: ٧]

‹‹ባንተም ላይ በወረቀት የተጻፈን መጽሐፍ ባወረድን እና በእጆቻቸው በነኩት ኖሮ...›› *( አል አንዓም፡ 7)*

መጽሐፉንና መጻፊያውን የተለያዩ ነገሮች አድርጎ ገለጻቸው፡፡ የተፈጠሩ ብዕሮች በተፈጠሩ ቀለሞች ብጽፉትም እንኳ ቁርአን የእርሱ ንግግር መሆኑን እንዲህ ስል ያረጋግጣል፡፡

﴿وَلَوۡ أَنَّمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ مِن شَجَرَةٍ أَقۡلَٰمٞ وَٱلۡبَحۡرُ يَمُدُّهُۥ مِنۢ بَعۡدِهِۦ سَبۡعَةُ أَبۡحُرٖ مَّا نَفِدَتۡ كَلِمَٰتُ ٱللَّهِ﴾ [لقمان: ٢٧]

‹‹ከዛፍም በምድር ያለው ሁሉ ብእሮች ቢሆኑ ኖሮ ባህሩም ከእርሱ (ማለቅ) ቡኃላ ሰባት ባህሮች የሚጨመሩለት ሆኖ (ቀለም ሆኖ ብጻፍባቸው) የአላህ ቃላት ባላለቀች ነበር፡፡›› *(ሉቅማን ፡ 27)*

﴿قُل لَّوۡ كَانَ ٱلۡبَحۡرُ مِدَادٗا لِّكَلِمَٰتِ رَبِّي لَنَفِدَ ٱلۡبَحۡرُ قَبۡلَ أَن تَنفَدَ كَلِمَٰتُ رَبِّي وَلَوۡ جِئۡنَا بِمِثۡلِهِۦ مَدَدٗا﴾ [الكهف: ١٠٩]

‹‹ባህሩ ለጌታዬ ቃላት (መጻፊያ) ቀለሞች በሆነ ኖሮ ብጤውን ጭማሪ ብናመጣም እንኳን የጌታዬ ቃላት ከማለቋ በፊት ባህሩ ባለቀ ነበር›› በላቸው፡፡ *(አልካህፍ፡ 109)*

ብእሮች የጻፉት ሆነ ያልጻፉት ሁሉም እኩል የአላህ ንግግሮች ናቸው፡፡

የአላህ ንግግር ፍጡር ነው ያለ ሰው በእርግጥም ከዷል፡፡ ምክንያቱም ንግግሩ ከባህሪያቱ መካከል አንዱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በፍጥረታቱ እና በንግግሩ መካከል እንዲህ በማለት ለያይቶ ይናገራል፡፡

﴿إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ يُغْشِى ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ يَطْلُبُهُۥ حَثِيثًا وَٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ وَٱلنُّجُومَ مُسَخَّرَٰتٍۭ بِأَمْرِهِۦٓ ۗ أَلَا لَهُ ٱلْخَلْقُ وَٱلْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ﴾ [الأعراف: ٥٤]

ጌታችሁ ያ ሰማያትን እና ምድርን በስድት ቀናት ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፡፡ ከዚያም በዐርሹ ላይ ተደላደለ፡፡ (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲሆን ይሸፍናል፡፡ ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲሆኑ (ፈጠራቸው)፡፡ ንቁ! ማዘዝና መፍጠር የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡ *(አል አዕራፍ፡ 54)*

በፍጥረታቱ (ሰማያት፣ ምድር፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት) እና በትህዛዙ (ፍጥረታቱን ባስገኘበት ትህዛዙ) መካከል مُسَخَّرَاتٍ بِأَمْرِهِ (በትእዛዙ የተገሩ ሲሆኑ) በማለት ለያየ፡፡

አላህ ከንፈር፣ ሚላስ፣ ጉሮሮ፣ ላንቃን የመሳሰሉትንና እንቅስቃሰያቸውንም ጭምር በመፍጠር የቁርአን አንባቢዎችን ድምጽ ፈጠረ፡፡ ይህ ደግሞ የሚሰማው ነገር የአላህ ቃል መሆኑን ውድቅ አያደርግም፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿أَفَتَطْمَعُونَ أَن يُؤْمِنُوا۟ لَكُمْ وَقَدْ كَانَ فَرِيقٌ مِّنْهُمْ يَسْمَعُونَ كَلَٰمَ ٱللَّهِ ثُمَّ يُحَرِّفُونَهُۥ مِنۢ بَعْدِ مَا عَقَلُوهُ وَهُمْ يَعْلَمُونَ﴾ [البقرة: ٧٥]

‹‹ከእነርሱ የሆኑ ጭፍሮች የአላህን ቃል የሚሰሙና ከተረዱት ቡኃላ እነርሱ እያወቁ የሚለውጡት ሲሆኑ...›› *(አልበቀራህ፡ 75)*

ሌላ ሰው ቢያነበውም የሚሰማው ነገር የአላህ ቃል ነው፡፡ አንዳንድ ምሁራን እንዳሉት፡-

«الصوت صوت القاري والكلام كلام الباري».

‹‹ድምጹ የአንባቢው ድምጽ ነው፡፡ ንግግሩ የአላህ ንግግር ነው፡፡››

# ክፍል ስምንት

ከቁርኣን እና ከሐዲስ ምንጮች እንደዚሁም ከትክክለኛ አዕምሮ በመነሳት ትክክለኛው ሸሪዓ ይታወቃል፡፡ ከቁርኣንና ሐዲስ ውጪ አዕምሮ ብቻውን አይጠቅምም፡፡ ያለ አዕምሮም ቁርኣንና ሐዲስ አይጠቅሙም፡፡ ከሁለቱ አንዳቸው በመታጣታቸው ሐቅን የማወቅ ዕድል ይታጣል፡፡ በግልጽ ተቃርነው ከተገኙ ቁርኣንና ሐዲስ ተቀዳሚ ይደረጋሉ፡፡ ምክንያቱም ቁርኣንና ሐዲስ ሙሉ የሆነው ፈጣሪ እውቀት ሲሆን አዕምሮ ደግሞ ውስን የሆነው የፍጡር እውቀት ነውና፡፡ አዕምሮ እንደ ዓይን ሲሆን ቁርኣንና ሐዲስ ደግሞ እንደ ብርሃን ነው፡፡ የዓይን ብርሃን ያለው ሰው በድቅድቅ ጨላማ በዓይኑ መጠቀም አይችልም፡፡ አዕምሮ ያለው ሰውም ያለመለኮታዊ ራእይ በአዕምሮው መጠቀም አይችልም፡፡ ዓይን የሚመረው በብርሃን ልክ ሲሆን አዕምሮ ደግሞ በመለኮታዊ ራእይ ልክ ይመራል፡፡ እኩለቀን ላይ በደንብ ማየት እንደሚቻለው ሁሉ መለኮታዊ ራእይ እና አዕምሮ ሙሉ ሲሆኑ ትክክለኛውን መንገድ መከተል እና አርቆ አሳብነትም የተሟላ ይሆናል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿أَوَمَن كَانَ مَيۡتٗا فَأَحۡيَيۡنَٰهُ وَجَعَلۡنَا لَهُۥ نُورٗا يَمۡشِي بِهِۦ فِي ٱلنَّاسِ كَمَن مَّثَلُهُۥ فِي ٱلظُّلُمَٰتِ﴾ [الأنعام: ١٢٢]

‹‹ሙት የነበረ እና አድነነው በሰዎች መካከል የሚራመድበትን ብርሃን ያደረግንለት ሰው ከእርሷ መውጣት የማይችል ሆኖ ጨለማዎች ውስጥ እንዳለ ሰው ብጤ ነውን?›› *(አልአንዓም: 122)*

ምድር ላይ የሚኳዙ እንሰሳት እና በራሪ አዕዋፋት ባላቸው እውቀት መሠረት አንድ ጊዜ እየተኳዙ ሌላ ጊዜ እያረፉ፣ ወገናቸውንና ሀገራቸውን ለይተው፣ ጎጆዋቸውን ሰርተው፣ ጠላታቸውን ለይተው አውቀው እንደሚሉት አዕምሮ ያለው ሰውም በዚህች ዓለም በአዕምሮው ይጠቀማል፡፡

ነገር ግን ለየት ባለ ሁኔታ የሰው ልጅ ነብዩ (ሰዐወ) ላይ በወረደው ራእይ ካል ሆነ በቀር በአዕምሮው ብቻ ወደ ጌታው መንገድ መመራት አይችልም፡፡ ምክንያቱም ያለ መለኮታዊ ራእይ ፅልመት ውስጥ ነውና፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ٱللَّهُ وَلِيُّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ يُخۡرِجُهُم مِّنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِۖ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَوۡلِيَآؤُهُمُ ٱلطَّٰغُوتُ يُخۡرِجُونَهُم مِّنَ ٱلنُّورِ إِلَى ٱلظُّلُمَٰتِ﴾ [البقرة: ٢٥٧]

‹‹አላህ የነዚያ ያመኑት ረዳት ነው፡፡ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል፤ እነዚያም የካዱት ወዳጆቻቸው ጣዖታት ናቸው፤ ከብርሃን ወደ ጨለማዎች ያወጧቸዋል፡፡ ...›› *(አልበቀራህ፡ 257)*

‹‹ያወጣቸዋል›› አለ፡፡ ምክንያቱም ከእርሱ ውጪ ጨለማ ውስጥ ናቸውና፡፡ እሳት እና ብርሃን እየተባለ ዓይነቱ ብለያይም ብርሃን አንድ እንደሆነው ሁሉ ቁርኣንና ሱና እየተባለ ዓይነቱ ብለያይም መለኮታዊ ራእይም አንድ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ ﴾ [النساء: ٥٩]

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህን ታዘዙ መልዕክተኛውንም ታዘዙ፤...›› *(አልንሳእ፡ 59)*

አንድ ሰው በአዕምሮው ብቻ ወደ አላህ መንገድ መመራት ይችላል ያለ ሰው ያለ ብርሃን ወደ ፈለገበት መንገድ በዓይኑ ብቻ መመራት ይችላል እንዳለ ሰው ነው፡፡ ሁለቱም በግልጽ የሚታወቁትን ነገር የካዱ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ሀይማኖት የሌለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዱንያ የለውም፡፡

አላህ መለኮታዊ ራእዩን ሁሉም ፍጥረት የሚመሩበት ብርሃን ብሎ ጠራው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِهِۦ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَٱتَّبَعُواْ ٱلنُّورَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ مَعَهُۥٓ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴾

[الأعراف: ١٥٧]

‹‹እነዚያም በእርሱ ያመኑ፣ ያከበሩትም፣ የረዱትም፣ ያንንም ከእርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ እነዚያ እነሱ የሚዲኑ ናቸው፡፡›› *(አልአዕራፍ፡ 157)*

እሱ ነው ነቢያትን እና ተከታዮቻቸውን (ወደ ትክክለኛው መንገድ) የሚመራው፡፡

አላህ ያዘዘውን በመታዘዝ ከከለከለውም ነገር በመከልከል ለትዕዛዙ እናድራለን፤ የተናገረውን እውነት ብለን እንቀበላለን፤ ምክንያቱን ካወቅን እናምናለን፡፡ ባናውቅም እናምናለን እንታዘዛለን፡፡ መታወቅ የሚችሉ ነገሮች ሆነውም እንኳ ሁሉም ሰው እኩል የማያውቃቸው ነገሮች አሉ፡፡ ታዲያ የሰው አዕምሮ የማይደርስባቸው ነገሮች ሆነው እያሉ እንዴት ሁሉም ሰው ማወቅ አለበት ይባላል?

‹አላህ ከወሰናቸው ነገሮች ከተረዳው እና ከገባኝ ነገር ውጪ አልቀበልም፡፡ በአዕምሮ የማይደረስበትን ነገር አላምንበትም› ያለ ሰው ከመለኮታዊ ምንጮች አዕምሮን አስቀድሟል፡፡ ነገር ግን ልደርስበት ያልቻለው እሱ ነው እንጂ አዕምሮ ያልደረሰበትን ነገር የለም ማለት አይቻልም፡፡ ዓይን መመልከት የሚችልበት ሪቀት የተገደበ

እንደመሆኑ መጠን አዕምሮም የራሱ ጥግ አለው፡፡ ከዚያ ማለፍ አይችልም፡፡ ስለዚህ ተፈጥሮ ዓይን የደረሰበት ድረስ ብቻ ነው ከዚያ ቡኃላ ፍጥረት የምባል ነገር የለም ማለት አይቻልም፡፡ ጆሮም የመስማት ኃይሉ የተገደበ ነው፡፡ ስለዚህ ጆሮአችን ያልደረሰባቸውን ድምጾች የሉም ማለት አንችልም፡፡ ለመሳሌ፡ ጉንዳን ድምጽ አለው፤ ነገር ግን አይሰማም፡፡ እንደዚሁም በፍጥረተዓለሙ ውስጥ ትላልቅ እና ግዙፍ ፍጥረታት፣ ከዋክብት፣ ሌሎችም የማይታዩ ፍጥረታት አሉ፡፡

# ክፍል ዘጠኝ

ህግ ማውጣት ለአላህ ብቻ የተገባ ነው፡፡ የፈለገውን ይፈቅዳል፤ የፈለገውን ይከለክላል፡፡ ይህንን የሚያደርገው በእውቀት እና በጥበብ ነው፡፡ የእርሱ ህግ ለሀይማኖትም ለዚህች ዓለምም የሚበጅ ሆኖ ነው የመጣው፡፡ የእርሱ ትዕዛዝም ሆነ ክልከላው በአንድ ዘመን ወይም በአንድ ቦታ በተናጠል ለአቅመ አዳም ከደረሱ ሰዎች በፈቃዱ ቢሆን እንጂ አይነሳም፡፡

ሀይማኖትንም ሆነ የዚህችን ዓለም ህይወት አስመልክቶ ያወጣቸውን ህጎች አንለያያቸውም፡፡ እያንዳንዳቸውም ዱኒያዊና ዓይማኖታዊ ግዴታዎች ናቸው፡፡

- ዓይማኖታዊ የሚባሉት፡- ሰላት፣ ፆም፣ ሐጅ፣ ዝክር፣ መስጂድ መገንባት የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- ዱኒያዊ የሚባሉት፡- ግብይት፣ ጋብቻ፣ ፍች፣ ውርስ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በመካከላቸው የለየ ሰው ዓይማኖታዊ ውሳኔዎችን ለአላህ አድርጎ የዚህችን ዓለም ውሳኔ ደግሞ ለሌላ አካል አድርጓል፡፡ ስለዚህም ክዷል ይባላል፤ ምክንያቱም የትኛውም ህግ የእርሱ ብቻ ነውና፡፡ ከእርሱ ውጪ ላሌ ነገር ተገቢ ያደረገ ሰው ሱጁድን ከእርሱ ውጪ ላለ ነገር እንዳደረገ ሰው ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنِ ٱلۡحُكۡمُ إِلَّا لِلَّهِۚ أَمَرَ أَلَّا تَعۡبُدُوٓاْ إِلَّآ إِيَّاهُۚ﴾ [يوسف: ٤٠]

‹‹ፍርዱ የአላህ እንጂ የሌላ አይደለም፡፡ እርሱን እንጂ ሌላን እንዳትገዙ አዟል፡፡›› *(ዩሱፍ: 40)*

የእስራኢል ልጆችም የካዱት በዚህ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ٱتَّخَذُوٓاْ أَحۡبَارَهُمۡ وَرُهۡبَٰنَهُمۡ أَرۡبَابٗا مِّن دُونِ ٱللَّهِ وَٱلۡمَسِيحَ ٱبۡنَ مَرۡيَمَ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا
لِيَعۡبُدُوٓاْ إِلَٰهٗا وَٰحِدٗاۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ سُبۡحَٰنَهُۥ عَمَّا يُشۡرِكُونَ﴾ [التوبة: ٣١]

‹‹ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለሌውን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን የመርየምን ልጅ አልመሲሕን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፡፡ እርሱ እነሱ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው፡፡›› *(አልተውባ: 31)*

ሥራቸውንም ሽርክ ብሎ ጠራው፡፡ አላህ መጽሐፉን አውርዷል፡፡ ህጉንም ደንግጓል፡፡ ህጎቹ የተደነገጉበትን ሁኔታን እና ዘመን እኩል እንደሚያውቀውና እንደሚመለከተው ሁሉ የሚመጡ ነገሮችንና ያለፉ ክስተቶችንም ያውቃል፡፡ ቀደም ብሎ ያለፈ ስለሆነ ወይንም ወደፊት የሚከሰት ነገር በመሆኑ እውቀቱ አንድ የተከሰተን ነገር አስመልክቶ ጎደሎ አይሆንም፡፡ አሁን የተከሰተ በመሆኑም አይጨምርም፡፡ እርሱ ዘንድ ያለፈውም፣ የወደፊቱም፣ የአሁኑም፣ የሩቁም እውቀት እኩል ናቸው፡፡ ጥራት እና ሊቅና ተገባው!

‹የአላህ ፍርድ ለወረደበት ጊዜ ብቻ የሚመጥን ነው፤ ከዚያ ውጪ ላለው ጊዜ ግን ሰዎች ከአላህ ፍርድ ጋር ባይስማማም ይበጃል ብለው ያሰቡትን ህግ ማውጣት ይችላሉ› ያለ ሰው አባባሉ ክህደት ነው፡፡ ይህንን የሚል ሰው የሰዎች እውቀት የሚታየውን እና የማይታዩን ነገር አስመልክቶ ይለያያል፤ ስለዚህ ይህንን ተከትሎ ፍርዱም ይለያያል ማለቱ ነው፡፡ ይህ ሰው አላህም እንደዚያ (እንደሰዎቹ) መስሎታል፡፡ የሰው ልጅ እርሱ ጋር በቅርብ ያለውን እውቀቱን ራእይ ስወርድ በነበረበት ጊዜ ከነበረው አላህ ስለሩቅ እውቀት ካለው እውቀት ያስቀድማል፡፡ ይህ ደግሞ ክህደት ነው፡፡ ማጋራትም ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የቅርቡንና የሩቁን ነገር እኩል ያውቃል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿عَـٰلِمِ ٱلْغَيْبِ وَٱلشَّهَـٰدَةِ فَتَعَـٰلَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ﴾ [المؤمنون: ٩٢]

‹‹የሩቁን እና የቅርቡን ሁሉ አዋቂ (በእርሱ) ከሚያጋሩትም ሁሉ ከፍ አለ፡፡›› *(አል ሙእሚኑን፡ 92)*

የአላህ ፍርድ የአሁን ያለውና የሩቁ አንድ ናቸው፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿قُلِ ٱللَّهُمَّ فَاطِرَ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ عَـٰلِمَ ٱلْغَيْبِ وَٱلشَّهَـٰدَةِ أَنتَ تَحْكُمُ بَيْنَ عِبَادِكَ فِى مَا كَانُوا۟ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ﴾ [الزمر: ٤٦]

‹‹የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ የሩቁን እና የቅርቡን አዋቂ አላህ ሆይ! አንተ በባሮችህ መካከል የተወዛገቡበትን ጉዳይ አስመልክቶ (በሐቅ) ትፈርዳለህ በል፡፡›› *(አልዙመር፡ 46)*

ባሉትም በሌሉትም ባሮቹ መካከል ይፈርዳል፡፡

ሊበራሊዝሞች እንደሚሉት ሀይማኖታዊ ፍርድን እና ዓለማዊ ፍርድን ለይቶ አላህን ዓይማኖታዊ ህግ አውጪ ሰውን ዓለማዊ ህግ አውጪ ያደረገ ሰው በእርግጥም ብዙ ህግ አውጪዎችን አድርጓል፡፡ ህግ ማውጣት ደግሞ የአላህ ብቻ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿أَفَتُؤْمِنُونَ بِبَعْضِ ٱلْكِتَـٰبِ وَتَكْفُرُونَ بِبَعْضٍ﴾ [البقرة: ٨٥]

‹‹በመጽሐፉ በከፊሉ አምናችሁ በከፊሉ ትክዳላችሁን?›› *(አልበቀራህ፡ 85)*

በከፊሉ የካዱ ሰው በሁሉም ክዷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በሰዎች መካካል በመልዕክተኛው (ሰዐወ) ላይ በተወረደው ቁርኣንና ሐዲስ እንዲወሰን አዟል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَأَنِ ٱحۡكُم بَيۡنَهُم بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ وَلَا تَتَّبِعۡ أَهۡوَآءَهُمۡ وَٱحۡذَرۡهُمۡ أَن يَفۡتِنُوكَ عَنۢ بَعۡضِ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ إِلَيۡكَ﴾ [المائدة: ٤٩]

‹‹አላህ ባወረደው ህግ በመካከላቸው ፍረድ፣ ፍላጎቶቻቸውንም አትከተል አላህ ወደ አንተ ካወረደው ከከፊሉ እንዳያሳስቱህ ተጠንቀቃቸው (ማለትን አወረድን)፡፡›› *(አልማኢዳ፡ 49)*

ለማለት የተፈለገው ስጨቃጨቁ እና ስካሰሱ ለማለት ነው፡፡

‹‹ማሳሳት/ፍትና/›› የተባለው ከአላህ (ሱ.ወ) ህግ መውጣት ነው፡፡

መለኮታዊው ራእይ በዝርዝር ያልገለጻቸውን ነገሮች ከተረጋገጠው የአላህ ውሳኔ ጋር በማይጋጭ ሁኔታ የእስላም ሊቃውንቶች ማብራራት ይችላሉ፡፡

የሰዎች ፍርድ እና ምርጫ ከአላህ ፍርድ ጋር ከተቃረነ ከአላህ ውሳኔ ተቀዳሚ አይደረግም፡፡ የህዝብ ውሳኔ ተቀዳሚ የሚደረግ ቢሆን ኖሮ ነቢያት ከሐቅ ውጪ በሆኑ ነበር፤ ምክንያቱም ያደጉት እና የኖሩት ስህተት በሆነ ነገር ላይ በተስማሙ ህዝቦች መካከል ወይንም አብዛኞቻቸው የተሳሳቱ የሆኑ ህዝቦች መካከል ነበርና፡፡

# ክፍል አስር

አላህ (ሱወ) ፍጥረታቱን ከመፍጠሩ በፊት ልካቸውን ወስኗል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَخَلَقَ كُلَّ شَيْءٍ فَقَدَّرَهُۥ تَقْدِيرًا﴾ [الفرقان: ٢]

‹‹ነገሩንም ሁሉ የፈጠረና በትክክልም ያዘጋጀው ነው፡፡›› *(አልፉርቃን: 2)*

﴿إِنَّا كُلَّ شَيْءٍ خَلَقْنَٰهُ بِقَدَرٍ﴾ [القمر: ٤٩]

‹‹እኛ ሁሉን ነገር በልክ ፈጠርነው፡፡›› *(አልቀመር: 49)*

﴿وَكَانَ أَمْرُ ٱللَّهِ قَدَرًا مَّقْدُورًا﴾ [الأحزاب: ٣٨]

‹‹የአላህም ትዕዛዝ የተፈረደ ፍርድ ነው፡፡›› *(አል አሕዛብ: 38)*

አላህ ጥሩውንም መጥፎውንም ውሳኔ ወስኗል፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ትክክለኛ ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«وتؤمن بالقدر خيره وشره». رواه مسلم

‹‹ (የአላህ) ውሳኔን ጥሩሁንም መጥፎውንም  ታምናለህ፡፡››

አላህ የወሰነውን ውሳኔ ማወቁ የግድ ነው፤ ምክንያቱም የአንድ ነገርን ልክ መወሰን የሚችለው ስለዚያ ነገር የሚያውቅ አካል ብቻ ነው፡፡ የዚያን ነገር ዝርዝር ጉዳይ እና ምስጥር፣ ቦታውን፣ ወዴት መለወጥ እንደሚችል፣ ጅምሩን፣ ማብቂያውን፣ ወዘተ ከፈጠረው አካል ውጪ ማንም አያውቅም፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿لِتَعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ وَأَنَّ ٱللَّهَ قَدْ أَحَاطَ بِكُلِّ شَيْءٍ عِلْمًۢا ﴿١٢﴾﴾ [الطلاق: ١٢]

‹‹አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መሆኑን አላህም በነገሩ ሁሉ በእውቀት ያካበበ መሆኑን ታውቁ ዘንድ (ይህንን አሳወቃችሁ)፡፡›› *(አልጠላቅ:12)*

እንዲህም ይላል፡-

﴿أَلَا يَعْلَمُ مَنْ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلْخَبِيرُ﴾ [الملك: ١٤]

‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ እውቀተ ረቂቁ ውስጥ አዋቂው ሲሆን (ምስጥርን ሁሉ) አያውቅምን?›› *(አልሙልክ፡ 14)*

የነገሮችን ልክ መወሰኑን ያልተቀበለ ሰው አዋቂነቱንም አልተቀበለም ማለት ነው፡፡ አዋቂነቱን ያልተቀበለ ሰውም የነገሮችን ልክ መወሰኑን አልተቀበለም ማለት ነው፡፡ የነገሮች ልክ እርሱ ዘንድ በመጽሐፍ ውስጥ ተጽፏል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿مَّا فَرَّطۡنَا فِي ٱلۡكِتَٰبِ مِن شَيۡءٖۚ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّهِمۡ يُحۡشَرُونَ﴾ [الأنعام: ٣٨]

‹‹በመጽሐፉ ውስጥ ምንንም ነገር አልተውንም፡፡›› *(አልአንዓም፡ 38)*

﴿وَكُلَّ شَيۡءٍ أَحۡصَيۡنَٰهُ فِيٓ إِمَامٖ مُّبِينٖ﴾ [يس: ١٢]

‹‹ነገሩንም ሁሉ ገላጭ መሪ በሆነ መጽሐፍ ውስጥ አጠቃለልነው፡፡›› *(ያሲን፡ 12)*

አፈጣጠሩ በሁለት ይከፈላል

- የተገራና አማራጭ ያልተሰጠው፡ ለምሳሌ፡- ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብትን የመሳሰሉ
- አማራጭ የተሰጣቸው፡ ለምሳሌ፡- ሰው፣ ጅን፣ መላእክት የመሳሰሉት ሲሆኑ ያለምርጫቸው እንዲንቀሳቀሱ እና ወንጀል እንዲሰሩ ካስገደዳቸው ቡኃላ በወንጀሉ ምክንያት አይቀጣቸውም፡፡ እንደዚያውም ከእርሱ ጋር በሥራ እና በፍላጎት ተጋሪ ይሆኑ ዘንድ ያለችሎታ አማራጭ ብቻ አልሰጣቸውም፡፡ ነገር ግን በፍላጎቱ ስር የተገደበን ፍላጎት አደረገላቸው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنۡ هُوَ إِلَّا ذِكۡرٞ لِّلۡعَٰلَمِينَ ٢٧ لِمَن شَآءَ مِنكُمۡ أَن يَسۡتَقِيمَ ٢٨ وَمَا تَشَآءُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلۡعَٰلَمِينَ﴾ [التكوير: ٢٨ – ٢٩]

‹‹እርሱ የዓለማት መገሰጫ እንጂ ሌላ አይደለም፤ ከእናንተ ቀጥተኛ መሆንን ለሻ ሰው (መገሰጫ ነው)፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻም አትሹም፡፡›› *(አልተክዊር፡ 27-29)*

አላህ ባሮችንና የሚሰሩትንም ሥራ ፈጥሯል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿قَالَ أَتَعۡبُدُونَ مَا تَنۡحِتُونَ ٩٥ وَٱللَّهُ خَلَقَكُمۡ وَمَا تَعۡمَلُونَ﴾ [الصافات: ٩٥ – ٩٦]

‹‹(እብራሂም) የምትጠርቡትን ትገዛላችሁን አላቸው፡፡ አላህ እናንተንም የምትሰሩትንም የፈጠረ ሲሆን›› *(አልሳፋት፡95፣96)*

አላህ ምክንያትን ፈጠረ፤ ምክንያትም እንዲትሆን አደረገ፤ በእሷ ምክንያት የተገኘውንም ነገር እንዳስገኘው ሁሉ፡፡ ይህ ፍጥረተዓለሙ በምን ሁኔታ ላይ መሆን እንዳለበትና እንዴት መጓዝ እንዳለበት አስመልክቶ የእውቀቱን ስፋትና የላቀ ጥበቡን የሚያሳይ ነው፡፡

አዕምሮ የአላህን ውሳኔ (ቀደርን) አስመልክቶ ምስጥሩ ወይንም ትክክለኛ ምንነቱ ስላልገባው ብቻ ከማመን መቆጠብ የለበትም፡፡ ከአላህ ጥበቦች መካከል አዕምሮ ችሎ የማይሸከመው ጥበብ አለ፡፡ ምክንያቱም አዕምሮ እንደ ዕቃ ሲሆን አንዳንድ ጥበቦች ደግሞ እንደ ባህር ውሃ ነው፤ ዕቃ አይችላቸውም፡፡ ልክ እንደዚሁ ዓይን በጠራራ ፀሐይ ወደ ፀሐይ ለረዥም ሰዓት ብመለከት ቃጠሎን እንጂ ምንም እንደማይጠቀመው ሁሉ አንዳንድ ጥበቦችም ወደ አዕምሮ ብደርሱ እና አዕምሮ ለብዙ ሰዓታት ብያስተነትነውም ግራ ከመጋባት ውጪ ምንም አይጠቀምም፡፡

# ክፍል አስራ አንድ

ሞት ሐቅ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿كُلُّ مَنْ عَلَيْهَا فَانٍ ٢٦ وَيَبْقَىٰ وَجْهُ رَبِّكَ ذُو الْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ﴾ [الرحمن: ٢٦ – ٢٧]

‹‹በእርሷ (በምድር) ላይ ያለው ሁሉ ጠፊ ነው፤ የልቅናና የልግስና ባለቤት የሆነው የጌታህ ፊት ይቀራል (አይጠፋም)፡፡›› *(አልራሕማን፡ 26፣27)*

ከሞት ቡኃላ በሚመጡ ነገሮች፡- የቀብር ውስጥ ፈተና እና ቅጣት፣ የቀብር ውስጥ ድሎት በመሳሰሉት ማመን ከኢማን ይቆጠራል፡፡

❁ ሞቶ መቀስቀስ እንዳለ ማመንም ከኢማን ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَنُفِخَ فِي الصُّورِ فَإِذَا هُم مِّنَ الْأَجْدَاثِ إِلَىٰ رَبِّهِمْ يَنسِلُونَ﴾ [يس: ٥١]

‹‹በቀንዱም ይነፋል፤ ወዲያው እነርሱ ከመቃብሮቻቸው ወደ ጌታቸው በፊጥነት ይገሰግሳሉ፡፡›› *(ያሲን፡ 51)*

ያስተባበለ ሰው ይቅርና ይህንን የሚጠራጠር ሰው እንኳ በአላህ የካዴ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَأَمَّا الَّذِينَ كَفَرُوا أَفَلَمْ تَكُنْ آيَاتِي تُتْلَىٰ عَلَيْكُمْ فَاسْتَكْبَرْتُمْ وَكُنتُمْ قَوْمًا مُّجْرِمِينَ ٣١ وَإِذَا قِيلَ إِنَّ وَعْدَ اللَّهِ حَقٌّ وَالسَّاعَةُ لَا رَيْبَ فِيهَا قُلْتُم مَّا نَدْرِي مَا السَّاعَةُ إِن نَّظُنُّ إِلَّا ظَنًّا وَمَا نَحْنُ بِمُسْتَيْقِنِينَ﴾ [الجاثية: ٣١ – ٣٢]

‹‹እነዚያም የካዱትማ አንቀጾቼ በእናንተ ላይ ይነበቡ አልነበሩምን? ኮራችሁም፡፡ ከሃዲዎች ህዝቦችም ነበራችሁ፡፡ የአላህ ቀጠሮ እውነት ነው፤ ሰዓቲቱም በእርሷ (መምጣት) ጥርጥር የለም፡፡ በተባለ ጊዜም ሰዓቲቱ ምን እንደሆነች አናውቅም፤ መጠራጠርን የምንጠራጠር እንጂ ሌላ አይደለንም፤ እኛም አረጋጋጮች አይደለንም አላችሁ፡፡ (ይባላሉ)፡፡›› *(አልጃሲያ፡ 31፣32)*

﴿بَلْ كَذَّبُوا بِالسَّاعَةِ ۖ وَأَعْتَدْنَا لِمَن كَذَّبَ بِالسَّاعَةِ سَعِيرًا﴾ [الفرقان: ١١]

‹‹ይልቁንም በትንሳኤ አስተባበሉ፡፡ በትንሳኤ ላስተባበለ ሰው ሁሉ ነዳጅን እሳት አዘጋጅተናል፡፡›› *(አልፉርቃን፡ 11)*

❁ በሰሩት ሥራ መታሰብ እንዳለ ማመንም ከኢማን ነው፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَنَضَعُ ٱلۡمَوَٰزِينَ ٱلۡقِسۡطَ لِيَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ فَلَا تُظۡلَمُ نَفۡسٞ شَيۡـٔٗاۖ وَإِن كَانَ مِثۡقَالَ حَبَّةٖ مِّنۡ خَرۡدَلٍ أَتَيۡنَا بِهَاۗ وَكَفَىٰ بِنَا حَٰسِبِينَ﴾ [الأنبياء: ٤٧]

‹‹በትንሳኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን፡፡ ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም፡፡ (ሥራው) የሰናፍጭ ክብደት ያህል ቢሆንም እርሷን እናመጣታለን፡፡ ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ›› (የባሮቼን ስራ በመቆጣጠር እና በማወቅ እኔ በቂ ነኝ)፡፡ *(አል አንቢያእ፡ 47)*

❁ ሚንዳ እና ቅጣት፣ ጀነት እና እሳት መኖሪያቸውንም ማመን ከኢማን ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَأَمَّا ٱلَّذِينَ شَقُواْ فَفِي ٱلنَّارِ لَهُمۡ فِيهَا زَفِيرٞ وَشَهِيقٌ﴾ [هود: ١٠٦]

‹‹እነዚያ እድለቢሶቹማ (ከሃዲዎችማ) በእሳት ውስጥ ናቸው፡፡ ለእነርሱ በእሷ ውስጥ ማናፋት እና መንሰቅሰቅ አላቸው፡፡›› (ሁድ፡ 106)

﴿وَأَمَّا ٱلَّذِينَ سُعِدُواْ فَفِي ٱلۡجَنَّةِ﴾ [هود: ١٠٨]

‹‹እነዚያም እድለኞቹማ ጀነት ውስጥ ናቸው፡፡›› *(ሁድ፡ 108)*

ከሀዲያን የእሳት ሲሆኑ አማኞች ደግሞ የጀነት ናቸው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَأَمَّا ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فَأُعَذِّبُهُمۡ عَذَابٗا شَدِيدٗا فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِ وَمَا لَهُم مِّن نَّٰصِرِينَ ۝٥٦ وَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَيُوَفِّيهِمۡ أُجُورَهُمۡۗ وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ ٱلظَّٰلِمِينَ﴾ [آل عمران: ٥٦-٥٧]

‹‹እነዚያ የካዱትንማ በቅርቢቱ ዓለም እና በመጨረሻው ዓለም ብርቱ ቅጣትን እቀጣቸዋለው፡፡ ለእነርሱም ምንም ረዳቶች የሏቸውም፡፡ እነዚያም ያመኑትማ መልካም ሥራዎችንም የሰሩት ምንዳዎቻቸውን ይሞላላቸዋል፡፡ አላህም በዳዮችን አይወድም፡፡›› *(ኣሊእምራን፡ 56፣57)*

❁ የመጨረሻውን ቀን (ቂያማን) አስመልክቶ መለኮታዊ ራእይ ያረጋገጣቸውን ነገሮች ባጠቃላይ ማመን ከኢማን ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ስራጥ (ጀሃነም ላይ የተዘረጋ ድልድይ)፣ ሚዛን፣ ሐውድ[1]፣ የጥሩ ስራ እና የመጥፎ ስራ መዝገቦች የመሳሰሉትን ማመን፡፡

❁ ❁ ❁

1 አላህ (ሱ.ወ) ለነቢያችን (ሰዐወ) የሰጣቸው ትልቅ ውሃ ሲሆን ከእርሱ የጠጣ ሰው ፈጽሞ ጥማት አያገኘውም፡፡ ከወተት በላይ ነጭ ሲሆን መጠጫዎቹ እንደ ሰማይ ክዋክብት የበዙ ናቸው፡፡ የጎን ስፋቱ አንድ ወር ያስኬዳል፡፡

# ክፍል አስራ ሁለት

ከጀመዓ ጋር መሆን ግዴታ ነው፡፡ መሪ በለሌበት ጀመዓ አይኖርም፡፡ አላህን ለመታዘዝ ስባል የሙስሊሞችን መሪ መታዘዝ ግድ ይላል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ وَأُوْلِي ٱلۡأَمۡرِ مِنكُمۡ ﴾ [النساء: ٥٩]

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ አላህን ታዘዙ መልዕክተኛውንም ታዘዙ፡፡ ከእናንተ የሆኑ ባለስልጣናትንም (ታዘዙ)፡፡›› *(አልኒሳእ፡ 59)* ከእናንተ ማለቱ ከሙስሊሞች ለማለት ነው፡፡

ካፊር መሪ መሆን ትክክል አይደለም፡፡ ለእሱ ቃል መግባትም አይቻልም፡፡ እሱን መታዘዝም ለሰዎች ጥቅም ካልሆነ በቀር ለእሱ ጥቅም ስባል ግዴታ አይደለም፡፡

መሪው እውቀት ያለው (ዓልም) ባይሆን ዓይማኖታዊ እና ዓለማዊ ጉዳዮች ፈር እንዲይዙ ስባል ዓልም ጋር መስራት አለበት፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَإِذَا جَآءَهُمۡ أَمۡرٞ مِّنَ ٱلۡأَمۡنِ أَوِ ٱلۡخَوۡفِ أَذَاعُواْ بِهِۦۖ وَلَوۡ رَدُّوهُ إِلَى ٱلرَّسُولِ وَإِلَىٰٓ أُوْلِي ٱلۡأَمۡرِ مِنۡهُمۡ لَعَلِمَهُ ٱلَّذِينَ يَسۡتَنۢبِطُونَهُۥ مِنۡهُمۡ ﴾ [النساء: ٨٣]

‹‹ከጸጥታ ወይም ከፍርሃት አንዳዎች (ወሬ) በመጣላቸውም ጊዜ እርሱን ያጋንናሉ፡፡ ወደ መልክተኛውና ከእነርሱ ወደ ትዕዛዙ ባለቤቶች (ወደ አዋቂዎቹ) በመለሱት ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ (ነገሩን) የሚያውጣጡት ባወቁት ነበር፡፡›› *(አልኒሳእ፡ 83)* ከዓልሞች ሌላ ማንም አያውቅም፡፡

እሱ ላይ በአመጽ መውጣት አይፈቀድም፡፡ ትዕዛዙን እምቢ ማለት እና ከእርሱ ጋር መጨቃጨቅም አይፈቀድም፡፡ ግልጽ የሆኔ ክህደትን እስካልፈጸመ ድረስ በምፈጽማቸው በደሎች ላይ ትዕግስት ይደረጋል፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ ኡምሰለማ (ረ.ዐ) ነብዩ (ሰዐወ) እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፋለች፡-

«انه يستعمل عليكم أمراء فتعرفون وتنكرون فمن كره فقد برئ ومن أنكر فقد سلم ولكن من رضي وتابع. قالوا: يارسول الله ألا نقاتلهم؟ قال: لا ما صلو». رواه مسلم

‹‹መሪዎች በእናንተ ላይ ይሾማሉ፡፡ (ከሚሰሩት ስራ) ኸይር መሆኑን የምታውቁት አለ፡፡ ሐራም መሆኑንም የምታውቁት አለ፡፡ ሐራሙን የተቃወመ ሰው በእርግጥም (አላህ ፊት ከመጠየቅ) ነፃ ወጣ፡፡ ነገር ግን የወደደ ሰው እና የተከተለ (እሱ ወንጀለኛ ነው)፡፡››

ቂምን ለመበቀል ሳይሆን ክፉቱን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ሲባል በእውቀት እና በጥበብ ይመከራል፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ ተሚሙ-ዳሪ (ረ.ዐ) ነብዩ (ሰዐወ) እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፏል፡-

أن النبي صلي الله عليه وسلم قال: «الدين النصيحة». قلنا لمن؟ قال: «لله، ولكتابه، ولرسوله، ولأئمة المسلمين، وعامتهم». رواه مسلم.

ነብዩ (ሰዐወ) ‹‹ዲን ማለት መልካም ማሰብ ነው››፡፡ አሉ፡፡ ‹‹ለማን?›› ብለን ጠየቅናቸው፡፡ ‹‹ለአላህ፣ ለመጽሐፉ፣ ለመልዕክተኛው፣ ለሙስሊም መሪዎችና ለሁሉም ሙስሊሞች ነው›› አሉ፡፡

ነውሩን መከታተል፣ ደካማ ጎኑን ወይም እሱን ብቻ የሚመለከቱ ስህተቶቹን ማጋለጥ እንደዚሁም ወንጀሎቹን እና ድክመቱን ማሰራጨት አይፈቀድም፡፡ እነዚህን በተመለከተ ለብቻ ይመከራል፡፡ የተከለከለን (ሐራም የሆነን) ነገር ለሰዎች ብፈቅድ እና ብያስፋፋ እና ዓልሙ ይህንን ነገር ሌላ ሰው ሳይሰማ (ለመሪው) ለብቻ ብነግረው ከስህተቱ ይመለሳል ያጠፋውንም ነገር ያስተካክላል ብሎ ካመነ ለብቻ እሱን መምከር እና መገሰጽ ግዴታ ይሆንበታል፡፡ ካልሆነ ግን ሸሪዓው እንዳይለወጥ እና ሀይማኖቱም እንዳይቀየር ስባል መሪው ለሰዎች የፈቀደው መጥፎ ስራ በሸሪዓ የተከለከለ መሆኑን ለሰዎች ግልጽ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ይህን ለሰዎች ግልጽ ማድረግ የእምነቱና የእምነታቸው ሐቅ ከመሆኑም በተጨማሪ ለእነርሱ ልደረግላቸው ከሚገቡ ‹‹ነሲሓ›› (መልካም ምክሮች) መካከል ግዴታ የተደረገ ነገር በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ‹‹ለአላህ፣ ለመጽሐፉ፣ ለመልዕክተኛው፣ ለሙስሊም መሪዎችና ለሁሉም ሙስልሞች ነው›› ከተባለው ይመደባል፡፡ ይህም የህዝብ ሐቅ ተቀዳሚ ስለ ምደረግ ነው፡፡

አዋቂ ራሱን ከሰዎች ጉዳይ እና ጥቅማቸውን ከሚያስጠብቅላቸው ነገር ገለልተኛ ማድረግ የለበትም፡፡ ከዚህች ዓለም ጥቅማ ጥቅም ፍላጎት ማጣቱ ተወዳጅ የሚሆነው እሱን ብቻ በሚመለከቱ ጥቅማ ጥቅሞች ላይ ነው፡፡ ሰዎች በዚህች ዓለም ከሚያገኙት ጥቅማ ጥቅም ፍላጎት ማጣቱ ግን ተወዳጅ ወይም የተወደሰ አይደለም፡፡ ስለዚህ በአንዲት ድርሃም[1] እንኳ ብትሆን የተበደለን ሰው ጥብቅና ይቁም (ይርዳ)፡፡ የተራበ ሰው አንድ ተምር እንኳ ቢሆን እንድበላ ይታገል፡፡ ምክንያቱም ዓልም አላፍነት አለበትና፡፡ ሰዎች ዱንያቸው ማማሩ ለዲናቸው ማማር በር ይሆናል፡፡ ነብዩ (ሰዐወ) ለካበተ ሐብት አላጎበደዱም፡፡ ይህም ከመሆኑ ጋር ለበሪራ እና ለሌሎች ሰዎች በጢቂት ዲናሮች (የወርቅ ሳንቲሞች) ምክንያት ይከራከሩላቸው ነበር፡፡ ይህንንም አስመልክቶ በሰዎች መካከል ቆመው ንግግር ያደርጉ ነበር፡፡

1 የብር ሳንቲም ነው፡፡

# ክፍል አስራ ሦስት

ጅሃድ እስከ ቂያማ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ቁርኣን እስካለ ድረስ አንድም ቀን እንኳ ሳይሻር የተረጋገጠ ሆኖ ምድር ላይ ይቆያል፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ ከጃብር (ረ.ዐ) ነብዩ (ሰዐወ) እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-

«لا تزال طائفة من أمتي يقاتلون على الحق ظاهرين الى يوم القيامة». رواه مسلم.

‹‹ከህዝቦቼ አንድ ቡድን እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ የበላዮች ሆነው ሐቅ ላይ የሚታገሉ አይጠፉም፡፡››

የተከሰተውን ችግር ከማስወገድ እና ከመመለስ ውጪ የመከላከል ጅሃድ ላይ የመሪውን ፍቃድ መጠየቅ ወይም የኒያ መስተካከል መስፈርት አይሆንም፡፡ ይህ ደግሞ ከራስ ክብር ወይም ከነፍስ ወይም ከንብረት መከላከል እንኳ ቢሆን ግዴታ ነው፡፡ ቡኻሪ እና ሙስሊምን ጨምሮ አቢዳውድ፣ ትርሚዚ፣ ነሳኢ እና እብን ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«من قتل دون ماله فهو شهيد، ومن قتل دون أهله، أو دون دمه، أو دون دينه، فهو شهيد».

‹‹ከንብረቱ ስከላከል የተገደለ ሰው እርሱ ሰማእት ነው፡፡ ከቤተሰቡ ወይም ከደሙ ወይም ከሃይማኖቱ ስከላከል የተገደለ ሰውም እርሱ ሰማእት ነው››፡፡

በሰው ክብር፣ በነፍስና በንብረት ላይ ወረራ የሚፈጽምን ሰው መመለስና መከላከል ግዴታ ነው፡፡ ወራሪው ሙስሊም ቢሆንም ባይሆንም፡፡ ነሳኢ በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ ቃቡስ ከአባታቸው እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ሰዐወ) መጥቶ፡- አንድ ሰው ገንዘቤን (ልዘርፍ) ፈልጎ ወደ እኔ ይመጣል (ምን ማድረግ አለብኝ)? አላቸው፡፡ በአላህ ገስጸው አሉት፡፡ ‹‹ባይገሰጽስ››? አለ፡፡ ‹‹በዙሪያህ ያሉ ሙስሊሞችን በእሱ ላይ እንዲያግዙህ ጠይቃቸው›› አሉ፡፡ ‹‹ከሙስልሞች አንድም ሰው በዙሪያዬ ባይኖርስ››? አለ፡፡ ‹‹አሚሩ እንድረዳክ ጠይቅ›› አሉ፡፡ ‹‹አሚሩ ከእኔ ርቆ ቢሆንስ››? አለ፡፡ ‹‹ለኣኽራቸው ስሉ ከተሰው ሰዎች እስክትሆን ወይም ገንዘብህን እስከታተርፍ ድረስ ለገንዘብህ ስትል ተጋደል›› አሉ፡፡

ለፍሊጋ በሚደረግ ጅሃድ ላይ የአላህን ቃል ከፍ ለማድረግ መነየት መጋደል ግዴታ ነው፡፡ ቡኻሪ እና ሙስሊም ከአቢ ሙሳ አል አሽዐሪይ እንዳስተላለፉት፡- ‹‹አንድ የገጠር

ነዋሪ የሆነ ሰው መጥቶ፡- `የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አንድ ሰው ለምርኮ ስል ይዋጋል፤ አንዱ ደግሞ ለዝና ይዋጋል፣ አንዱ ደግሞ ያለውን ሚና ለማሳየት ይዋጋል፤ ታዲያ ማን ነው በአላህ መንገድ የተዋጋው´? (ብሎ ጠየቀ)፡፡ የአላህ መልዕክተኛም፡- ‹‹የአላህ ቃል ከፍ ያለች እንዲትሆን የተዋጋ ሰው፤ እሱ ነው በአላህ መንገድ የተዋጋ›› አሉ፡፡

በዚህ ዓይነት ጅሃድ ላይ መሪውን መታዘዝ ግዴታ ነው፡፡ በወንጀል እስካላዘዘ ድረስ የምለውን መስማት እና መታዘዝ ግድ ይላል፡፡ ቡኻሪ እና ሙስሊም ከአቡሁረይራ (ረ.ዐ) እንዲህ የምል አስተላልፈዋል፡- የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ)፡- ‹‹የታዘዘኝ ሰው በእርግጥም አላህን ታዟል፤ ትዕዛዜን የጣሰ ሰው በእርግጥም የአላህን ትዕዛዝ ጥሷል፤ አሚረን የታዘዘ ሰው በእርግጥም እኔን ታዟል፤ አሚረን ያልታዘዘ ሰው በእርግጥም እኔን አልታዘዘም፡፡›› ብለዋል፡፡

# ክፍል አስራ አራት

ከነቢያት ቀጥሎ በላጭ ህዝብ የነብዩ (ሰዐወ) ሰሓቦች ናቸው፡፡ ያላቸውን ደረጃ አስመልክቶ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿مُّحَمَّدٞ رَّسُولُ ٱللَّهِۚ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ أَشِدَّآءُ عَلَى ٱلۡكُفَّارِ رُحَمَآءُ بَيۡنَهُمۡۖ تَرَىٰهُمۡ رُكَّعٗا سُجَّدٗا يَبۡتَغُونَ فَضۡلٗا مِّنَ ٱللَّهِ وَرِضۡوَٰنٗاۖ سِيمَاهُمۡ فِي وُجُوهِهِم مِّنۡ أَثَرِ ٱلسُّجُودِۚ ذَٰلِكَ مَثَلُهُمۡ فِي ٱلتَّوۡرَىٰةِۚ وَمَثَلُهُمۡ فِي ٱلۡإِنجِيلِ كَزَرۡعٍ أَخۡرَجَ شَطۡـَٔهُۥ فَـَٔازَرَهُۥ فَٱسۡتَغۡلَظَ فَٱسۡتَوَىٰ عَلَىٰ سُوقِهِۦ يُعۡجِبُ ٱلزُّرَّاعَ لِيَغِيظَ بِهِمُ ٱلۡكُفَّارَۗ وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ مِنۡهُم مَّغۡفِرَةٗ وَأَجۡرًا عَظِيمَۢا﴾ [الفتح : ٢٩]

‹‹ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው፡፡ እነዚያም ከእርሱ ጋር ያሉትም ከሃዲያን ላይ ብርቱዎች፣ በመካከላቸው አዛኞች ናቸው፡፡ አጎንባሾች ሰጋጆች ሆነው ታያቸዋለህ፤ ከአላህ ችሮታንና ውዴታን ይፈልጋሉ፤ ምልክታቸው ከስግደታቸው ፈለግ ስትሆን በፊቶቻቸው ላይ ናት፤ ይህ በተውራት ውስጥ (የተነገረው) ባህሪያቸው ነው፤ በእንጂልም ውስጥ ምሳሌያቸው ቀንዘሉን እንዳወጣ አዝመራ እና (ቀንዘሉ) እንዳበረታው እንደወፈረምና ገበሬዎቹን የሚያስደንቅ ሆኖ በአገዳዎቹ ላይ ተስተካክሎ እንደቆመ (አዝመራ) ነው፤ (ያበረታቸውና ያበዛቸው) ከሃዲዎችን በነሱ ሊያስቆጭ ነው፤ አላህም እነዚያን ያመኑትንና ከነሱ በጎዎችን የሠሩትን ምህረትንና ታላቅ ምንዳን ተስፋ አድርጎላቸዋል፡፡›› *(አልፈትሕ፡ 29)*

ነቢያት እንደሚበላለጡት ሁሉ ሰሓቦችም ይበላለጣሉ፡፡ ከነቢያት መካከል በደረጃ ዝቅ የምለው ከሰሓቦች መካከል በደረጃ ከፍ የምለውን ይበልጣል፡፡ ከሰሓቦች በደረጃ ዝቅ የምለው ሰሓቦችን ተከትለው ከመጡ ትውልዶች መካከል በደረጃ ከፍ የምለውን ይበልጣል፡፡

ከሰሓቦች መካከል ከፍ ያለ ደረጃ ያላቸው በቅድሚያ ወደ እስላም የገቡት ናቸው፡፡ ምክኒያቱም እስላም ኃይል ሳይኖረው በፊት በነብዩ ያመኑት እስላም ኃይል ካገኘ ቡኃላ ካመኑት ይበልጣሉ፡፡ መካ በድል ከመከፈቷ በፊት ያመኑ ሰዎች ከተከፈተች ቡኃላ ካመኑት ይበልጣሉ፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿لَا يَسۡتَوِي مِنكُم مَّنۡ أَنفَقَ مِن قَبۡلِ ٱلۡفَتۡحِ وَقَٰتَلَۚ أُوْلَٰٓئِكَ أَعۡظَمُ دَرَجَةٗ مِّنَ ٱلَّذِينَ أَنفَقُواْ مِنۢ بَعۡدُ وَقَٰتَلُواْ﴾ [الحديد : ١٠]

‹‹ከእናንተ ውስጥ (መካ) ከመከፈቷ በፊት (ገንዘቡን) የለገሰና የተጋደለ ሰው (መካ ከተከፈተች ቡኃላ ከተዋጋና ከለገሰ ጋር) አይስተካከልም››:: *(አልሐዲደ: 10)*

ነገር ግን መካ ከተከፈተች ቡኃላ ያመኑትም የነብዩ ባልደረባ የመሆንን (የሰሓባነትን) እድል በማግኘት ቀደም ብለው ካመኑት ጋር ይህንን ደረጃ እኩል ይጋራሉ:: ምክኒያቱም ከተጠቀሰው የቁርኣን አንቀጽ ቀጥሎ አላህ እንደህ ብሏልና፡-

﴿وَكُلّٗا وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلۡحُسۡنَىٰۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ﴾ [الحديد : ١٠]

‹‹ለሁሉም አላህ መልካሚቱን ተስፋ ቃል ገብቶላቸዋል:: አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው››:: *(አልሐዲደ: 10)*

እንዲህም ይላል፡-

﴿وَٱلسَّٰبِقُونَ ٱلۡأَوَّلُونَ مِنَ ٱلۡمُهَٰجِرِينَ وَٱلۡأَنصَارِ وَٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُوهُم بِإِحۡسَٰنٖ رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهُمۡ وَرَضُواْ عَنۡهُ﴾ [التوبة : ١٠٠]

‹‹ከስደተኞቹና ከረዳቶቹም ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎች እነዚያም በበጎ ሥራ የተከተሏቸው አላህ ከእነርሱ ወዷል፤ እነርሱም ከርሱ ወደዋሉ››:: *(አልተውባ: 100)*

ከቀዳሚዎቹ መካከል በደረጃ የሚበልጡት፡- አስሩ በጀነት የተበሰሩት ሰዎች ናቸው:: ከእነሱም በላጮቹ፡- አራቱ ኸሊፋዎች ናቸው፤ ከዚያም የበድር ዘመቻ ላይ የተሳተፉ፣ ቀጥለው የእሁድ ዘመቻ ላይ የተሳተፉ፣ ቀጥለው ዛፏ ስር ቃል ከዳን የፈጸሙ ናቸው:: አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿لَّقَدۡ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ إِذۡ يُبَايِعُونَكَ تَحۡتَ ٱلشَّجَرَةِ فَعَلِمَ مَا فِي قُلُوبِهِمۡ فَأَنزَلَ ٱلسَّكِينَةَ عَلَيۡهِمۡ وَأَثَٰبَهُمۡ فَتۡحٗا قَرِيبٗا﴾ [الفتح : ١٨]

‹‹ከሙእሚኖቹ በዛፊቱ ስር ቃል ክዳን በሚጋቡህ ጊዜ አላህ በእርግጥ ወደደ:: በልቦቻቸውም ውስጥ ያለውን አወቀ:: በእነርሱም ላይ እርጋታን አወረደ:: ቅርብ የሆነንም መከፈት መነዳቸው››:: *(አልፈትሕ: 18)*

ቡኻሪ ጃብርን ጠቅሰው የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ)፡- ዛፊቷ ስር ቃል ክዳን ለገቡ ሰዎች ‹‹ምድር ላይ ካሉ ሰዎች እናንተ በላጮች ናችሁ››:: ማለታቸውን ዘግበዋል:: ቁጥራቸው አንድ ሺ አራት መቶ ነበር::

ሰሓቦች መለኮታዊ ራእይን የተሸከሙና ዲኑን ከነብዩ የሰሙ ሰዎች ናቸው:: እነርሱን

ማነወር የእምነቱን ሰንሰለት መቁረጥ ነው፤ የነብዩን (ሰዐወ) ሱና አስመልክቶም ጥርጣሬ እንድፈጠር ማድረግ ነው፡፡ ከነብዩ (ሰዐወ) ቀጥሎ የሚታመኑት እነሱ ናቸው፡፡

ሙስሊም በሰሒሕ ኪታባቸው ከአቡ ሙሳ (ረ.ዐ) እንዲህ የምል አስተላልፈዋል፡-

‹‹እኔ ለህዝቦቼ ታማኝ ነኝ፤ በሄድኩ ጊዜ ሰሓቦቼ ላይ (ከፈተና) የተቀጠሩት ነገር ይመጣባቸዋል፤ ሰሓቦቼ ለህዝቦቼ ታማኝ ናቸው፤ ሰሓቦቼ ሲሄዱ (ከፈተና) ለህዝቦቼ የተቀጠሩት ነገር ይመጣባቸዋል፡፡››

ከስህተት የተጠበቁ ግን አይደሉም፡፡ ስህተታቸውን ሰበብ አድርጎ እነርሱን ማስነወር ግን አይፈቀድም፡፡ በመካከላቸው የነበረውን አለመግባባት ከመድገም (ሕያው ከማድረግ) መራቅ ያስፈልጋል፡፡ ከግጭቱ የሚወሰዱ ትምህርታዊ ነገሮችን በአክብሮትና ምክኒያታቸውን በምንቀበልላቸው መልኩ ማየት ይኖርብናል፡፡ ሰሓቦች በመካከላቸው አለመግባባት ብኖርም እንኳ ከእነሱ ቡኃላ ከመጡ ሰዎች ይበልጣሉ፡፡ ከእነሱ ውጪ ያሉ ሰዎች አንድነት ብኖራቸውም እንኳ፡፡ ምክኒያቱም አላህ ደረጃቸውን ያላቀው እርስ በርስ ባላቸው ወዳጅነት ሳይሆን ለነብዩ ጥሩ ወዳጅ በመሆናቸው ነው፡፡ በመካከላቸው የነበረው አለመግባባት ሐቅን በመፈለግ ያደረጉት ስለሆነ ብሳሳቱም ሰዋብ ያገኛሉ፡፡ ከነብዩ (ሰዐወ) ጋር መወዛገብ ወንጀል ነው፡፡ ከዚህ አላህ አጥርቷቸዋል፡፡ እንዲሁም ጥሩ ባልደረቦች ሆነው ከሌሎች ብልጫ አግኝተውበታል፡፡

የሰሓቦችን ክብር መጉደፍ በር ስለሆነ በአንዳቸው ከተከፈተ በተቀሩት ላይም ይከፈታል፡፡ ለዚህም ነው ከእነሱ ቀጥሎ የተገኙ ትውልዶች እና ተከታዮቻቸው በሰሓቦች መካከል የተከሰተውን ግጭት አስመልክቶ ዝምታን የመረጡት፡፡

ዑመር ብን ዐብድልዐዚዝ ስለ ዐሊይ እና ዑስማን እንዲሁም ስለ ጀመልና ሲፊን ጦርነቶች ተጠይቀው ፡- ‹‹እሷ አላህ ከእሷ እጀን የጠበቃት ደም ነች፡፡ እኔ ምላሰን እሷ ውስጥ መንከር እጠላለሁ›› ብለዋል፡፡

ከነሱ ቡኃላ የምመጣ ሰው በቂያማ ቀን የሚጠየቀው በመካከላቸው ስለተከሰተው አለመግባባት ሳይሆን ከፍ ያለ ደረጃ እንዳላቸው አረጋግጧል ወይስ አላረጋገጠም የምለውን ነው፡፡

# ክፍል አስራ አምስት

በወንጀል ምክንያት አንድንም ወደ ቅብላ ዞሮ የሚሰግድን ሰው ካፍር ነው አንልም፤ ክህደት ካልፈጸመ በቀር፡፡ ከክህደት መካከል አንዱ አላህን መሳደብ ነው፡፡

እሱን መሳደብ ከሽርክ የከፋ ነው፡፡ ምክንያቱም ሙሽሪክ አላህን ወደ ድንጋይ ደረጃ ዝቅ አላደረገም፤ ነገር ግን ድንጋይን ነው ወደ አላህ ደረጃ ከፍ ያደረገው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ تَٱللَّهِ إِن كُنَّا لَفِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ٩٧ إِذۡ نُسَوِّيكُم بِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴾ [الشعراء: ٩٧ – ٩٨]

‹‹በአላህ እንምላለን፤ እኛ በግልጽ መሳሳት ውስጥ ነበርን፤ በዓለማት ጌታ ባስተካከልናችሁ ጊዜ››፡፡ *(አልሹዐራእ፡ 97፣98)* (ይህንን የሚሉት ለጣዖቶቹ ነው)፡፡

አላህን የተሳደበ ሰው ከድንጋይ ደረጃ በታች ዝቅ አድርጎታል፡፡

እሱን መሳደብ ትልቅ ክህደት ነው፡፡ ክህደት እንደ ኢማን ይጨምራል፤ ይቀንሳልም፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّمَا ٱلنَّسِيٓءُ زِيَادَةٞ فِي ٱلۡكُفۡرِ﴾ [التوبة: ٣٧]

‹‹የአንዱን ወር ክብር ወደ ሌላው ማዘግየት በክህደት ላይ (ክህደትን) መጨመር ነው››፡፡ *(አልተውባ፡ 37)*

እንዲህም ይላል፡-

﴿إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بَعۡدَ إِيمَٰنِهِمۡ ثُمَّ ٱزۡدَادُواْ كُفۡرٗا لَّن تُقۡبَلَ تَوۡبَتُهُمۡ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلضَّآلُّونَ ﴾ [آل عمران: ٩٠]

‹‹ እነዚያ ከእምነታቸው ቡኋላ የካዱ ከዚያም ክህደትን የጨመሩ ጸጸታቸው ፈጽሞ ተቀባይነት የላትም፡፡ እነዚያም የተሳሳቱ እነርሱ ናቸው››፡፡ *(ኣሊ ዒምራን፡ 90)*

መቀነሱና መጨመሩ ከእሳት አያወጣውም፤ ነገር ግን ቅጣቱን ልያከብድ እና ልያቀል ይችላል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ زِدۡنَٰهُمۡ عَذَابٗا فَوۡقَ ٱلۡعَذَابِ بِمَا كَانُواْ يُفۡسِدُونَ ﴾

[النحل:٨٨]

‹‹እነዚያ የካዱ፣ ከአላህ መንገድ የከለከሉ ያጠፉ በነበሩት ምክንያት ቅጣትን በቅጣት ላይ ጨመርንላቸው››፡፡ *(አልነሕል፡ 88)*

አላህና መልዕክተኛው ከመሰከሩለት ውጪ ለአንድም ሰው በተናጠል የጀነት ነው፤ የእሳት ነው ብለን አንመሰክርም፡፡ አማኝ ሆኖ የሞተ ሰው የጀነት መሆኑንና ከሃዲ (ካፍር) ሆኖ የሞተ ሰው የእሳት መሆኑን እንመሰክራለን፡፡

# ክፍል አስራ ስድስት

ትክክለኛ ነጻነት፡ ከአላህ ውጪ ለየትኛውም አካል ባሪያ ያለመሆን ነው፡፡ ከአላህ ትዕዛዝ መውጣትን እንደ ነጻነት መቁጠር ነፍስን ማምለክ እና ለስሜት ተገዢ መሆን ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፦

﴿أَفَرَءَيۡتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلۡمٖ وَخَتَمَ عَلَىٰ سَمۡعِهِۦ وَقَلۡبِهِۦ وَجَعَلَ عَلَىٰ بَصَرِهِۦ غِشَٰوَةٗ فَمَن يَهۡدِيهِ مِنۢ بَعۡدِ ٱللَّهِۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ﴾ [الجاثية: ٢٣]

‹‹ስሜቱን አምላኩ አድርጎ የያዘንና አላህም ከእውቀት ጋር ያጠመመውን፣ በመስሚያውና በልቡ ላይ ያሸገበትን፣ መመልከቻው ላይም ሽፋንን ያደረገበትን ሰው አየህን?›› ከአላህ ቡኃላስ ማን ያቀነዋል? አትገሰጹምን?›› (አልጃሲያ፡ 23)

አንድ ሰው የፈለገውን ነገር በፈለገው ሁኔታና በፈለገው ጊዜ መናገር እና መስራት ይችላል ያለ ሰው ለስሜቱና ለሰይጣን ባሪያ መሆኑን እያረጋገጠ ነው፡፡ ሰው ባሪያ ሆኖ ነው የተፈጠረው፤ ስለዚህ አላህን ካላመለከ ከእሱ ውጪ ላሌ ነገር ባሪያ መሆኑ አይቀርም፡፡

ምድር ላይ አንድ ሰው ብቻ ብኖር አላህ የተለያዩ ሸርዓዊ ቅጣቶችን አይወስንበትም ነበር፡፡ ለምሳሌ፦ ሰውን በመግደሉ ምክኒያት መግደልን፣ ሰውን በዝሙት ብሳደብ (መገረፍን)፣ በዝሙት ወንጀል መቀጣትን፣ የማትፈቀድለትን ሴት ከማየት ዓይኑን ሰበር ማድረግን እና ውርስ የመሳሰሉት አይወሰኑበትም ነበር፡፡

ዝሙት መስራት እና ወለድ መብላትን ጨምሮ ሌሎችንም ወንጀሎች አይከለከልም ነበር፡፡ እነዚህ ነገሮች ግዴታ የተደረጉበትና ከወንጀልም የተከለከለው የእሱ ዓይነት ሰዎች ከእርሱ ጋር ስላሉ ነው፡፡ ከእርሱ ውጪ ያሉት በቁጥር ስጨምሩ ህይወትም ይበልጥ ስርዓት እንዲትይዝና መስማማት እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ ጨረቃ ብቻዋን ብትሆን ኖሮ አሁን ባለችበት ሁኔታ እንዲትጓዝ አይደረግም ነበር፡፡ አላህ ይህን ያደረገው ከፀሐይ፣ ከመሬት፣ ከክዋክብት፣.... ጋር እንዲትስማማ ነው፡፡ ፕላኔቶች በጨመሩ ቁጥር ሥርዓቱም ይጨምራል፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፦

﴿يُغۡشِي ٱلَّيۡلَ ٱلنَّهَارَ يَطۡلُبُهُۥ حَثِيثٗا وَٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ وَٱلنُّجُومَ مُسَخَّرَٰتِۭ بِأَمۡرِهِۦٓۗ أَلَا لَهُ ٱلۡخَلۡقُ وَٱلۡأَمۡرُۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلۡعَٰلَمِينَ﴾ [الأعراف: ٥٤]

(አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲሆን ይሸፍናል፡፡ ፀሐይንና ጨረቃንም ክዋክብትንም በትዕዛዙ የተገሩ ሲሆኑ (ፈጠራቸው)፡፡ ንቁ! ማዘዝ እና መፍጠር የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡ *(አል አዕራፍ፡ 54)*

﴿لَا ٱلشَّمۡسُ يَنۢبَغِي لَهَآ أَن تُدۡرِكَ ٱلۡقَمَرَ وَلَا ٱلَّيۡلُ سَابِقُ ٱلنَّهَارِۚ وَكُلّٞ فِي فَلَكٖ يَسۡبَحُونَ﴾ [يس: ٤٠]

‹‹ጸሐይ ጨረቃን ልትደርስበት አይገባትም፡፡ ሌሊትም ቀንን (ያለጊዜው) ቀዳሚ አይሆንም፡፡ ሁሉም በመዞሪያቸው ውስጥ ይዋኛሉ፡፡›› (ያሲን፡ 40)

የእስላም ህጎች ዓይማኖትንና ዓለማዊ ኑሮን ስርዓት ለማስያዝ ነው፡፡ ከአላህ ህግጋት መውጣት እችላለው ያለ ሰው የአላህን ቅጣት ለራሱ ተገቢው ያደርጋል፡፡

ወደ እስላም መግባት ግድ ነው፡፡ ከእስላም መውጣት ደግሞ ወደ ኋላ መመለስ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَن يَرۡتَدِدۡ مِنكُمۡ عَن دِينِهِۦ فَيَمُتۡ وَهُوَ كَافِرٞ فَأُوْلَٰٓئِكَ حَبِطَتۡ أَعۡمَٰلُهُمۡ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ﴾ [البقرة: ٢١٧]

‹‹ከእናንተም ውስጥ ከሀይማኖቱ የሚመለስና እርሱም ከሓዲ ሆኖ የሚሞት ሰው እነዚያ (መልካም) ሥራቸው በቅርቢቱም በመጨርሻይቱም ሀገር ተበላሸች፡፡ እነዚያም የእሳት ጓዶች ናቸው፡፡ እነርሱ በእሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡›› *(አልበቀራህ፡ 217)*

ለአላህ ባሪያ መሆን የፍጡር እና የፍጥረዓለሙ ድካ ነው፡፡ ከዚህ መውጣት ይቻላል ያለ ሰው በዚህ ጉዳይ አላመነም ማለት ነው፡፡ ይህ ሰው እንደ ሀገር ወይም እንደ ህግ ከተፈጥሮ ሥርዓት መውጣት ይቻላል ብሎ አያምንም፤ ነገር ግን ከአላህ ባሪያነት ስር ግን መውጣት ይቻላል ይላል፡፡ ይህ ሰው በተዘዋዋሪ ፊጡር የተፈጠረበትን ዓላማ ማወቅ ያለመቻሉን ወይም አዕምሮ እንደለሌው እየመሰከረ ነው፡፡

አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ﴾ [الذاريات: ٥٦]

‹‹ጋኔንንና ሰውንም ልገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡›› *(ዛሪያት፡ 56)*

በዚህች ዓለም ላይ ጋኔንንና ሰውን እሱን እንዲያመልኩት ያስገኘው ጌታ በመጨረሻው ዓለም ለህሳብ፣ ለሰዋብና ለቂጣት ያስገኛቸዋል፡፡

ዱንያችንን ኣኺራችንን አላህ ያሳምርልን!

የአላህ ሰላምና እዝነት በነብዩ፣ በቤተሰባቸውና በተከታዮቻቸው ላይ ይሁን!

IslamHouse.com

IslamHouseAM/ Bengali.IslamHouse islamhouse.com/am/

channel/UC0T_q-4JkqIMTfmxa1L3kTw

For more details visit
www.GuideToIslam.com

GUIDE TO ISLAM

contact us :Books@guidetoislam.com

GuidetoIslam.org Guidetoislam1 Guidetoislam www.Guidetoislam.com

المكتب التعاوني للدعوة وتوعية الجاليات بالربوة

هاتف: ٩٦٦١١٤٤٥٤٩٠٠+ فاكس: ٩٦٦١١٤٩٧٠١٢٦+ ص ب: ٢٩٤٦٥ الرياض: ١١٤٥٧


ISLAMIC PROPAGATION OFFICE IN RABWAH

P.O.BOX 29465 RIYADH 11457 TEL: +966 11 4454900 FAX: +966 11 4970126

# በዐቂዳ ዙሪያ

## የተጻፉ ክፍሎች

ዐቂደህ በኢስላም ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው ጉዳይ ነው ይህ መጽሃፍ ስለ ዐቂደህ መሰረታዊ ትምህርት በውስጡ ይዘዋል አንብበው ዕውቀት እንድቀስሙ ተስፋ እናደርጋለን።




IslamHouse.com